# መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያለው ቦታ ፡ በማብራሪያ የታገዘ ትርጉምና ትንተና

# (Reception of Ethiopic Enoch in Gəʿəz Literature: Annotated Translation and Textual Analysis)

ኃይለ ኢየሱስ አለባቸው ሞላው[1]

**ABSTRACT**

The book of Enoch is one of the ancient compositions, which exists centuries before the birth of Christ and preserved only in Gəʿəz language while it has been lost, for over 2,000 years in the world. Currently, Scholars of philology, ancient history, and Second Temple Judaism, and the Origins of Christianity are interested in studying the Ethiopic Book of Enoch. However, their primary objective is not to investigate the position of Enoch in Ethiopic literatures rather to enhance their knowledge of Jewish folklore and to seek information upon the religious ideas of Judaism, especially concerning the Messiah. Above all, the Enochic scholars in the west judged the Book of Enoch as ‘book of idolatry and magical practice’.

The general objective of this study, therefore, is focused at exploring the role of 1Enoch in the production of medieval Gəʿəz texts and investigating the themes of Enochic readings by analyzing words, lines, stanzas, and paragraphs of Enochic writings which might indicate the Ethiopian socio-religious context in which the book has been transmitted and used. Hence, both prose and poetic manuscripts are consulted.

[1] ይህ ጽሑፍ ለ3ኛ ዲግሪ ማሟያ ከቀረበ የምርምር ሥራ ተቀንጭቦ የተወሰደ ነው፡፡ Haileyesus Alebachew Molaw (PhD), Samara University, Addis Ababa, Ethiopia haileeoc@gmail.com

Then, the quotations from Ethiopic Enoch explained in the light of the Book of Enoch accompanied by other liturgical and historical writings and annotated translations.

The result showed that the Book of Enoch was frequently referred and used as a source of Gəʻəz literatures like in Mäṣəḥäfä Məśṭir, Mäṣḥäfä Bahərəy, Mäṣḥäfä Bərhan, Mäṣḥäfä ṣäḥäy, Mäṣḥäfä Säʻatat, Dərsanä ’Ura ’el, Mäṣḥäfä Sənkəsar , ’Ärke, Mälkkə’ä Gubae and Qəne collections. The study, in general, showed that the fact that the presence of Ethiopic Book of Enoch in the Gəʻəz literature and the Book of Enoch itself doesn’t have to do with idolatry and magical practice. Rather, in the post- Enochic literature we find the manifestation of refined theological points of view about Trinity, Christology and Mariology.

*Keywords: Reception, Ethiopic Enoch, Gəʻəz Literature,*

# ፩. መግቢያ

መጽሐፈ ሄኖክ፦ ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዓለም ካበረከተቻቸው ቅርሶችና በመላው የዓለም ፈላስፎችና ምሁራን ዘንድ ከምትታወቅባቸው መገለጫዎቿ አንዱ ነው፡፡ ይኽ ታላቅና ብርቅየ መጽሐፍ በመላው ዓለም ከኹለት ሺሕ ዓመታት በላይ ዱካው በጠፋበት ዘመን በሀገራችን ግን በግዕዝ ቋንቋ ተተርጉሞ ሊቃውንቶቻችን ሲያነቡት፣ሲያጠኑት፣ሲማሩበት፣ሲያስተምሩበትና ሲመራመሩበት ኑረዋል፡፡ ምዕራቡ ዓለም ግን ለብዙ ምዕት ዓመታት መጽሐፉን ማግኘትና ማጥናት አቅቶት ኖሮአል፡፡ በግሪክ ወይም በዕርዕ ቋንቋ ከተላለፈው የመጽሐፈ ሄኖክ ክፍል (20 በመቶ የኽል) በስተቀር[2]፣ ከመጽሐፈ ሄኖክ የተወሰዱ አጫጭር ጥቅሶችን ከማንበብ ውጭ ምዕራባውያን መጽሐፈ ሄኖክን የማንበብም ኾነ የማጥናት እድል በምልአት አላገኙም ነበር፡፡ ምንም እንኳ ያገኙት መረጃ ትክክለኛ ባይሆንም የመጽሐፈ ሄኖክን በኢትዮጵያ መኖር ለመጀመሪያ ጊዜ ፍንጭ ያገኙት በ17ኛው መቶ ክ.ዘ የመጀመሪያው አጋማሺ አካባቢ ነበር፡፡ ይኸውም በግብፅ ይኖር የነበረ ጊለስ ዲ ሎቼስ (Gilles de Loches) የተባለ የካፑቹን (Capuchin) ካቶሊካዊ መነኩሴ የሄኖክን ብራና (የግዕዙን ቅጂ) እንዳገኘው የሚገልጽ ድብዳቤ ጽፎ በ1633 እ.ኤ.አ ኒኮላስ-ክላውዴ ፋብሪ ዲ ፔሪስክ (Nicolas-Claude Fabri de Peiresc) ለታባለ ፈረንሳዊ ምሁር በመላኩ ነበር፡፡ ምሁሩም በጣም ከመደሰቱ የተነሳ በከፍተኛ ዋጋ ገዝቶ በ1636 እ.ኤ.አ በእጁ ካስገባ በኋላ ለመተርጎም ቢያስብም ከሸጠለት መነኩሴ ይኹንታን ባለማኘቱ ትክክለኛውን መጽሐፈ ሄኖክ እንዳገኘ በማሰብ እውነታውን ሳይረዳ ሞት ቀደመው፡፡ ከዚያም በ1681 እ.ኤ.አ ሂዮብ ሉዶልፍ (Hiob Ludolf) የተባለ ምሁር የተገኘው ብራና ራሱ መጽሐፈ ሄኖክ ሳይኾን ከመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅስን የያዘ መጽሐፈ ምሥጢረ ሰማይ ወምድር የሚባል መኾኑን አረጋገጠላቸው፡፡[3] ምዕራባውያን ትክክለኛወንና ሙሉውን መጽሐፈ ሄኖክ አግኝተው ማጥናት የሚችሉበት አጋጣሚ የተፈጠረላቸው በ18ኛው ምዕተ ዓመት መዝጊያ ገደማ ግድም ላይ ነው፡፡

ይኸውም በ1773 እ.ኤ.አ ጄምስ ብሩስ የተባለው የስኮትላንድ ተወላጅ 3 የመጽሐፈ ሄኖክ ብራናዎችን ወደ አውሮጳ በማስገባቱ ነው፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለብዙ ምዕት ዓመታት በኢትዮጵያ ብቻ ሲነበብና ሲጠና የቆየው መጽሐፍ በምዕራባውያንም ዘንድ ከፍተኛ ትኩረትን በመሳብ የመጠናት እድል አጋጠመው፡፡ ይኽንንም እውን ለማድረግ

[2] Abba Daniel Assefa, (2006) "Enochic Studies in our Time", Paper Presented at Addis Ababa University, Addis Ababa

[3] Ted M. Erho and Loren T. Stuckenbruck, "A Manuscript History of Ethiopic Enoch" *Journal for the study of thePseudepigrapha*, 2013,Vol 23, no.2

ምዕራባውያን መጽሐፉን ከግዕዝ ወደ እንግሊዘኛ፣ወደ ጀርመንኛና ወደ ፈረንሳይኛ፣ወደ ዕብራይስጥም ተረጕሙት። በአኹኑ ሰዓት በብዙየአውሮጳ ቋንቋዎች ተተርጕሞ ይገኛል።[4]

መጽሐፈ ሄኖክ ወደ አውሮጳ ከገባ በኋላ ለዘመናዊ ጥናት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው ጀርመናዊው ኦገስት ዲልማን (August *Dillmann*) ነበር። ዲልማን አምስት የግዕዝ ብራናዎችን ከማነጻጸሩም[5] በላይ እጅግ የሚጠቅም ትርጕምም አሳትሞአል። ከዲልማን በኋላ የመጡ ሊቃውንትም የጥንት ጽሑፎችን ሲያጠኑ በመጽሐፈ ሄኖክ ላይም ምርምራቸውን ቀጥለው ነበር።

# ፪. በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ የተደረጉ ምርምሮችና ውጤቶች አጭር ቅኝት

ከላይ እንደተጠቀሰው መጽሐፈ ሄኖክ ከግዕዝ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ከመተርጎሙ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁ በአሜሪካ፣ በአውሮፓና በእስራኤል የሚገኙ ታላላቅ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ዘርፈ ብዙ በኾነ መንገድ ያጠኑታል፤ ጉባኤም ዘርግተው ይወያዩበታል። የሚሰጡት ትኩረት ከምን ጊዜውም በላይ ከመጨመሩ የተነሣ ከ60 የማያንሡ ሊቃውንት በሄኖክ ስም በየኹለት ዓመቱ እየተሰበሰቡ በአውሮጳ ሲወያዩ፣ እንዲኹም ቁጥራቸው በርካታ የኾነ የድኅረ ምረቃ ተማሪዎችም በመጽሐፈ ሄኖክ

---

[4] መጽሐፈ ሄኖክ ከግዕዝ ወደ እንግሊዘኛ በተለያዩ ግለሰቦች ተተርጕሟል። ከነዚኽ ሥራዎች ውስጥ በ15ኛ ክፍለ ዘመን ብራና ላይ የተመሠረተውና በፕሮፌሰር ኤፍርም ይስሐቅ የተዘጋጀውን ትርጕም መጥቀስ እንችላለን፣ E. Isaac, « 1 (Ethiopic Apocalypse of) Enoch. A New Translation and Introduction », The Old Tesament Pseudepigrapha Vol. 1 (J. H. Charlesworth ed.), DoubleDay, 1983. በ20ያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ መጽሐፈ ሄኖክ በአማርኛም ታትሞአል። መጽሐፉም እንደ ግዕዙ በ108 ምዕራፎች ሳይኾን በ42 ምዕራፎች ተከፍሎአል። እርግጥ የአንድምታው ትርጕም መጽሐፈ ሄኖክ በ19ኛው ክፍለ ዘመንም ኾነ ከዚያም በፊት ወደ አማርኛ እንደተመለሰ ያመለክታል (Daniel Assefa 2006)።

[5] ይኽ በጥንታውያን ጽሑፎች የጥናት ዘርፍ ውስጥ *critical edition* ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ከዓላማውም አንዳንዶቹን ብንጠቅስ፣ በብራናዎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች መመርመር፣ ብራናዎችን ማዋገን፣ ታሪካቸውን ማጥናት፣ እንዲሁም የንባብ ቅደም ተከተልን በማውጣት የልዩነቶችን መንሥኤ ለማወቅ መሞከር ይገኙበታል (Daniel Assefa 2006)። ከዲልማን በኋላ ቻርልስ (እንግሊዛዊ) ብራናዎችን በማነጻጸር በተሻለ መልኩ ሒሳዊ ዕትም (*critical edition*) አዘጋጅቷል። Charles, R. H., *The Ethiopic Version of the Book of Enoch : Edited from Twenty-Three Mss. Together with the Fragmentary Greek and Latin Vesions*, Anecdota Oxoniensia, Semitic Series 11 ; Oxford, Clarendon, 1906. )። ኒብ ድግሞ ጥንታዊ ባልኾነ በአንድ ብራና ላይ የተመሠረተ ዕትም ማዘጋጀቱ ይታወሳል፣( M. A. Knibb, *The Ethiopic Book of Enoch : A New Edition in the Light of the AramaicDead Sea Fragments* (2 vols.), Oxford, Clarendon, 1978)። በአኹኑ ሰዓት የሚገኙት የመጽሐፈ ሄኖክ ብራናዎች ቍጥራቸው እጅግ ስለጨመረ ሊቃውንት አዲስ ሒሳዊ እትም እንደ ሚያስፈልግ ይጠቁማሉ (ዝኒ ከማሁ)።

ጥናት ዙሪያ በየኹለት ዓመቱ በአሜሪካ እንደሚሰበሰቡና መጽሐፉ በምልዓት ተጠብቆ የሚገኘውና የተላለፈው በግዕዝ ቋንቋ በመኾኑ ለጥናታቸው ጥራት ሲሉም ብዙ የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች የግዕዝ ቋንቋን እንደሚያጠኑ አባ ዳንኤል አሰፋ (2006) ያስረዳሉ፡፡

በአይሁድ ሃይማኖት ላይ ማለትም ቅድመ ልደተ ክርስቶስ (ቅ.ል.ክ) ከ3ኛው ክፍለ ዘመን አንሥቶ እስከ ክርስትና ሃይማኖት መነሻ ድረስ የነበረውን የአይሁድ እምነት፣ ባህልና ታሪክ የሚያጠኑ ሊቃውንት ለመጽሐፈ ሄኖክ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ፡፡እንዲኹም አያሌ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ማለትም በሐዋርያትና ድኅረ ሐዋርያት በተነሡ አበው ክታቦች ውስጥ እንዴት እንደ ተጠቀሰ፣በሌሎች ታሪካዊና ሥነ ጽሑፋዊ መዛግብት ውስጥ ያለውን ቦታ እና የጥንት ቋንቋዎችን፣ጥንታዊ የሥነ ፈለክ ወይም ሥነ ከዋክብት (አስትሮኖሚን) እና የመሳሰሉትን ፍሬ ነገሮች ለማጥናት ያለውን ፋይዳ የሚጠቁሙ ምርምሮችን ማካኼድና በሄኖክ ስም በሚጠራ መጽሔት ማሳተም ከጀመሩም ውለው ማደራቸውን ዳንኤል አሰፋ (2006) አብራርተዋል፡፡

ሐዋርያው ይሁዳ "ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የኾነ ሄኖክ እነሆ ጌታ በኹሉ ላይ ሊፈርድ ይመጣል… ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚኽ ደግሞ ትንቢት ተናገረ" (1፣14) በማለት የገለጸው መጽሐፈ ሄኖክ በዘመነ ሐዋርያት የነበረውን የከበሬታ ቦታ በግልጽ ያመለክታል፡፡

እንዲኹም ብዙ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስን አስመልክቶ "ወልደ እጓለእመሕያው/ የሰው ልጅ" በሚለው አገላለጽ ላይ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ጥናታዊ ግምታቸውን አስቀምጠዋል[6]፡፡ በጥንት ቤተ ክርስቲያን አበው ዘንድም ትልቅ ስፍራ እንደነበረው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ በኒክልስበርግ (Nickelsburg 2001) እንደተገለጸው ቀሌምንጦስ ዘሮም፣ ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ፣ ጠርጡሊስ (Tertullian)፣ አርጌንስ (Origen) እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡[7]

## ፫. ማን ጻፈው?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የሐዋርያውን የይሁዳን ምስክርነትና የሐዋርያውያን አበውን ትምህርትና ጽሑፎች መሠረት አድርገው መጽሐፉ የተጻፈው የአዳም ሰባተኛ ትውልድ በኾነው በነቢዩ ሄኖክ መኾኑን አምነው ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንደ አንዱ ቆጥረው ተቀብለውታል፡፡ ምዕራባውያን ያላቸው ምልከታ

[6] G. Boccaccini (ed.), Enoch and the Messiah Son of Man, Revisiting the Book of Parables, Grand Rapids, Eerdmans,2007. G. W. E, Nickelsburg, A Commentary on the Book of 1 Enoch, chapters 1–36 ; 81–108, Minneapolis, Fortress Press, 2001, 83-86. (በአባ ዳንኤል 2006 እንደተጠቀሰው)፡፡

[7] መጽሐፈ ሄኖክን በጽሑፎቻቸው ውስጥ የሚጠቅሱ የጥንት አባቶችንና ምሁራንን ስም በዝርዝር ለማወቅ በ Nickelsburg2001, 87-100 የተብራራውን መመልከት ጠቃሚ ነው፡፡

ግን ከዚኽ የተለየ ነው፡፡ የእነርሱ መላምት (Hypothesis) መጽሐፉ በተለያየ ዘመን የተጻፉ አምስት መጻሕፍቶችን አንድ ላይ የያዘ ሲኾን ጊዜውም ቅ.ል.ክ 300 ዓመት ጀምሮ እስከ 165 ቅ.ል.ክ እንደኾነ ያስባሉ[8]፡፡ ማን ጻፈው? ለሚለውም ያስቀመጡት መላምት የተለያየ ነው፡፡ የተወሰነውን ክፍል በሙት ባሕር አካባቢ ኩምራን(Qumran) በሚባል ቦታ ይኖሩ የነበሩ የኩምራን ማኅበረ-ሰብ (Qumran community) ኢሴኔ ወይንም ሀሲዲያን (Essene or Hasideans)[9] የሚባሉ ማኅበረ-ሰብ (community) ወይንም ደግሞ የእነርሱ ቅድመ አያቶች ሊኾኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ (Nickelsburg 2001፡65)፡፡ አንዳንዶቹ አጥኚዎች መጽሐፈ ሄኖክ በከፊል ጥንታዊ እንዳልኾነና ክርስቲያኖችም እንደጻፉት የተረዱና ለማስረዳትም የሞከሩ ነበሩ (J. T, Milik 1976)[10]፡፡ ይኹን እንጂ ይኽ አቋም በአኹኑ ወቅት ተቀባይነትን አጥቶአል፡፡ ምክንያቱም የዛሬ 71 ዓመት አካባቢ በኩምራን ዋሻዎች የተገኙ የብራና ጥቅሎች (Qumran Scrolls) ከ2000 ዓመታት በላይ እድሜን ያስቆጠሩ በመኾናቸውና የመጽሐፈ ሄኖክን ጥቅሶች ይዘው በመገኘታቸው መጽሐፉ በሐዲስ ኪዳን ሊቃውንት አለመጻፉን አረጋግጠዋል፡፡ የጥቅሎቹም መገኘት የመጽሐፈ ሄኖክን ጥንታዊነት ከማረጋገጥ ባሻገር በዕብራይስጥና በአራማይክ የተጻፉ አያሌ መጻሕፍትንም ለዓለም በማስተዋወቅ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ኾኖም፣ በዚኽ ግኝት ሊቃውንቱ እጅጉን ቢደሰቱም በኩምራን የተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ብራና በፈለጉት መጠን ሊያሠራቸው አልቻለም (አባ ዳንኤል 2006)፡፡ የተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ብራና ከግዕዙ ብራና ዘር (ንባብ) ጋር ሲነጻጸር ከጽሑፉ 5 በመቶ ብቻ ነበር ይዞ የተገኘው[11]፡፡

---

8 መጻሕፍቶቹንም ፦ስለ ረዓይት የሚናገረውን ክፍል the Book of the Watchers (1 Enoch 1–36)፣ በምሳሌ የሚናገረውን ክፍል the Book of Parables of Enoch (1 Enoch 37–71)፣ ስለ ሚጠተ ብርሃናት የሚናገረውን the Astronomical Book or Book of Luminaries (1Enoch 72–82)፣ የራዕዩን ክፍል the Book of Dreams (1Enoch 83–90), እና የመልእክቱን ክፍል the Epistle of Enoch (1Enoch 91–108) በማለት ፈርጀውታል (Nickelsburg 2001)፡፡ በዚኽ ጥናት ውስጥ ከመጽሐፈ ሄሔኖክየተጠቀሱት ምዕራፍና ቁጥሮች መሠረት ያደረጉት የግዕዙን መጽሐፈ ሄኖክ አከፋፈል ነው፡፡ ግዕዙ በ108 ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲኾን አማርኛውና አንድምታ ትርጓሜው 42 ምዕራፎች አሉት፡፡

9 እነዚኽ ሰዎች በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ከሚሰጠው መመርያ በማፈንገጥ በይሁዳ መቃቢስ (Judas Maccabeus) መሪነት የራሳቸውን መንገድ የመረጡ የአይሁድ እምነት ተከታዮች አንደኾኑ ይገመታል፡፡

10 ይህንን አቋም በአንክሮ ያቀረበው የፖላንድ አገር ተወላጅ የነበረው ሚሊክ ነው (J. T, Milik, *The Books of Enoch : AramaicFragments of Qumrân Cave 4*, Oxford, Clarendon, 1976)፡፡ እርሱም በዚኽ መላምቱና፣ለግዕዙ ዘርዕ/ ንባብ ይሰጥ
በነበረው ዝቅተኛ ግምቱ ከሊቃውንት ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበታል (አባ ዳንኤል 2006)፡፡

11 ይኽንን የመቶኛ ንጽጽር(Proportion) ያሰሉት ኡሌንዶርፍ እና ኒብ (Ullendorff and Knibb 1977:601) ሲኾኑ መነሻቸውም ሚልክ (Milik) የተባለው አጥኝ በዋሻዎቹ ውስጥ የተገኙትን አረማይክ ብራናዎች ከግዕዙ ቅጅ እና ከዚኽም ከዛም ከሰባበሰበው ከግሪኩ ቅጅ ጋር በማነጻጸር ያገኘውን ውጤት እንደገና በ "በሳል ቅኝት" (critical review) ማየት ነበር፡፡ የእርሱ ሥራ ከግዕዙ ይልቅ ለግሪኩ ቋንቋ ያደላ ስለነበር ግኝቱን የደመደመው "for the first book ofEnoch, the Book of Watchers, we can calculate that exactly 50 per cent of the text is covered by the Aramaicfragments; for the third, the Astronomical Book, 30 per cent; for the fourth, the Book of Dreams, 26 per cent; for the fifth, the Epistle of Enoch, 18 per cent" (Milik

# ፬. መጽሐፈ ሄኖክ "ከቅዱሳት መጻሕፍት ዓለም" ለምን ተገፋ?

መጽሐፈ ሄኖክ ምንም እንኳ በጥንታውያን አይሁዶችም ኾነ በጥንት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘንድ ታላቅ ከበሬታና በሰፊው የመነበብ እድል የነበረው ቢኾንም አኹን ግን በአይሁዶች ቤተ እምነትም ይኹን በምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተገፍቶ የመውጣትና ከቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር ውጭ የመኾን እድል ገጥሞታል። ይኽም በዘርፉ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን ትኩረት መሳቡና ለምን የሚለውን ጥያቄ ማስነሣቱ አልቀረም።በጥናታቸውም ያመለከቱት በተለያዩ ምክንያቶችና በኺደት (gradual) እንጂ ቅጽበታዊና አሐዳዊ በኾነ ምክንያት አልነበረም። ብሩክ አየለ[12] (2015፡134) በዚኽ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶችን በማሰባሰብ የሚከተሉትን ምክንያቶች አስቀምጧል። ለምሳሌ ከዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (from canon of the Hebrew Bible) እንዲወጣና እንደ ባእድ እንዲቈጠር ካደረጉት ምክንያቶች ዋና ምክንያት ተብሎ የሚታሰበው በምኩራቡ አካባቢ ያሉ ረበናት (rabbis) በተባሉ የካህናት ወገን (Priestly groups) እና ኢሴኔ ወይንም ሀሲዲክ (Essene, or Hasidic) በተባሉት ቡድኖች መካከል የተፈጠረው መለያየትና አለመግባባትን ተከትሎ የመጣ ሲኾን ይኽውም መጽሐፈ ሄኖክ በሀሲዲዎች ዘንድ ተቀባይነት ስላለውና እንዲኹም የተጻፈው በእነርሱ እንደኾነ ረበናት(rabbis) ስለሚያምኑ ከሙሴና ከነቢያት መጻሕፍት ጋር እንዳይቈጠርና ቦታ እንዳይኖረው ወስነዋል[13]። እንደ ኹለተኛ ምክንያት የሚወሰደውም መጽሐፈ ሄኖክ የተጻፈው አምስቱ መጻሕፍተ ሙሴን (Torah) በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ እንደ ምስክር (reference) በመጥቀስ ሳይኾን በራሱ እውነት (self-assertion) ላይ ተመሥርቶ በመኾኑ ይኽም የሙሴን ሕግ እንዳለመቀበል ወይንም እንደመካድ ስለተቈጠረበት ነው ("...Enochism was condemned because of its lack of belief in Moses' torah''[14]። ሦስተኛም በመጽሐፈ ሄኖክ ውስጥ ስለ ወደቁት መላእክት (Fallen angels) የተጠቀሰው በዘፍጥረት 6፥2-4 ላይ እንደተገለጸው "የእግዚአብሔር ልጆች" (Sons of God) መባል ሲኖርበት መላእክት ስለሚል ነገረ ሃይማኖትን (Theology) እንደሚያፋልስ በማሰብ አይሁድ መጽሐፈ ሄኖክን

---

1976:5) በማለት ነበር። (Milik, Jozéf T. 1976, The Books of Enoch: Aramaic Fragments of Qumran Cave 4, Oxford: Clarendon).

12 Bruk Ayele. "*1 Enoch* in *Jude* and in the EOTC "Canon": Developing an Adequate Insight in Second Temple Literature (STL) in the Various Ethiopian Churches for a Better Understanding of Each Other and for the Promotion of Ecumenism and Mutual Cooperation"(PhD Thesis: University of Kwazulu-Natal,2015).

13 ይኽም የኾነው ድ/ል/ክ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት አካባቢ ላይ ነው፤ በጊዜውም የአይሁድን እምነት ማእከል ይዘው ይመሩና ይወስኑ የነበሩት ረበናት ስለነበሩ መጽሐፈ ሄኖክን (ተቃዋሚዎቻቸው የሚቀበሉትን) ከእነርሱ የቀኖና መጻሕፍት ለማስወጣት መወሰን አይከብዳቸውም።

14 ይኽ አይነት አስተሳሰብ የተፈጠረባቸው መጽሐፉን የጻፈው ነቢዩ ሄኖክ መኾኑን ስለማያምኑና ስለማይቀበሉ ነው።

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር ውጭ አድርገውታል፡፡[15]

ከምዕራብና ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት (Western and Eastern Churches) በኩልም በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ሒሶች፣ጥያቄዎች እና ነቀፌታዎች መነሣት የጀመሩት በ3ኛው ምእተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ነው፡፡ ከመጽሐፈ ሄኖክ ፊታቸውን ለማዞር በቀዳሚነት የሚጠቀሱትም ጠርጡለስ[16] እና አርጌንስ (Tertullian and Origen) ሲኾኑ ከእነርሱ በኋላም ከፍተኛ ትቺትና ተጽዕኖ በማሳደር የሚታወቀው አው ግስቲኖስ (Augustine of Hippo) ነው፡፡ የሒሳቸው ዋና ማጠንጠኛም መላእክት በሥጋዊ ፍትወት የወደቁ ኾነው በመጽሐፉ መገለጡ ነው፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም መጽሐፉን ከጥንቆላና ከነገረ አጋንንት ጋር አያይዘው ስለሚፈርጁት ነው፡፡ የመጽሐፈ ሄኖክ ጥናት ውጤቶች ከሚጠቁሟቸው ነጥቦች መካከል ሌላው ጉዳይ ይኽ መጽሐፍ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ? እንዴት ሊስፋፋና የክብር ቦታን ሊያገኝ ቻለ? የሚለው ነው፡፡፡ ይኽን በተመለከተ ምንም እንኳ እርግጠኛ እና ግልጽ የኾነ ማስረጃ ማግኘት ባይችልም ኒክልስበርግ (Nickelsburg 2001) የሚከተሉትን መላምቶች አስቀምጧል፡፡ አንደኛ በ4ኛው መ.ክ.ዘ መጽሐፈ ሄኖክ በግብፅ በከፍተኛ ደረጃ የሚታወቅና የተስፋፋ የነበረ መኾኑን በመጥቀስ በዘመኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሹመው ከግብፅ የሚላኩ ጳጳሳት ይዘውት ሊመጡ እንደቻሉ ይገምታል (...the close ties between the Ethiopian Church and the patriarchate in Alexandria and the book's widespread and long-standing use in Egypt would have been a factor in the book's importation into Ethiopia)፡፡[17] ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላም መጽሐፉ እንዴት ተቀባይነትን እንዳገኘና ሊስፋፋ የቻለበትን ምክንያት ኒክልስበርግ ሊያስረዳ የሞከረው የመጽሐፈ ሄኖክን ይዘት ከኢትዮጵያ መልክአ ምድራዊና ሥርዓተ አምልኮ ጋር በማያያዝ ነው፡ እንደእርሱ መላምት መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ልዩ ልዩ ተራሮች፣ ኮረብቶችና ሸለቆዎች ስለሚናገር ኢትዮጵያ ደግሞ የእነዚኽ መልክአ ምድሮች ባለቤት ስለኾነች መጽሐፉ በቀላሉ ተቀባይነትን አግኝቶ ሊስፋፋ መቻሉን ይጠቁማል፡፡ ይኸውም መጽሐፉን የሚያነቡት (ኢትዮጵያውያን) ከሚያውቁት ከሀገራቸው መልክአ ምድር ጋር ተዛምዶ ስላገኙት በቀላሉ

15 ምክንያት ለማብዛት እንጂ የመጽሐፉን አስፈላጊነት ቢያምኑበት የኢ/ኦ/ተ/ዋ/ቤተ ክርስቲያን በአንድምታ እንደምታትተው የወደቁት መላእክት(Fallen angels) የሚ.ለውን ደቂቀ ሴት ብሎ መተርጎምና መጽሐፉን መቀበል ይቀልነበር፡፡

16 ጠርጡለስ ምንም እንኳ በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ጥያቄ ቢያነሣም ልክ እንደ ሐዋርያው ይሁዳ ሄኖክን ከነቢያት እንደ አንዱ የሚቀበልና መጽሐፈ ሄኖክም በነቢዩ ሄኖክ እንደ ተጻፈ የሚቀበል መኾኑን ኒክልስ በርግ ጽፏል (Nickelsburg (2001:89) ፡፡

17 እዚኽ ላይ አንባቢ ሊያነሣው የሚገባ ጥያቄ በ4ኛው መ.ክ.ዘ. መጽሐፈ ሄኖክ በግብፅ በከፍተኛ ደራጃ የተስፋፋና የሚታወቅ ከነበረ የመጽሐፉ ቅጅ (Copy) ወይንም ደግሞ አሻራው በዘመናዊቷ ግብጽ እንዴት ሊገኝ አልቻለም? ኒክልስበርግ ራሱ እንደሰጠን መረጃ ከኾነ በኮፕት ቤተ ክርስቲያን የአንድ መነኩሴ መካነ መቃብር (ከ8ኛው-12ኛው መ.ክ.ዘ እንደ ነበረ የሚገመት መቃብር) ውስጥ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈ የጴጥሮስ ወንጌል (Gospel of Peter) ከተባለ ከአንድ ቁንጽል (ጎደሎ) የብራና ጥቅል ጋር ከተገኘው የመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ ወይንም ጥቅስ እና ከቀደምት አሌክሳንደራውያን (Alexandrian) ሊቃውንት ጽሑፎች ላይ ከተገኙት አንዳንድ ጥቅሶች በቀር ወጥና ምሉዕ የኾነ መጽሐፈ ሄኖክ አልተገኘም፡፡

ተረዱትና ወደዱት ማለቱ ይመስላል፡፡ በተጨማሪም እንደ ኒከልስበርግ አረዳድ መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ልዩ ልዩ ዕፅዋትና እንስሳት ስለሚገልጽ ኢትዮጵያ ደግሞ የተለያዩ ብርቅየ እንስሳትና የዕፅዋት ዓይነቶች የሚገኙባት ሀገር በመኾኗ መጽሐፉ ተቀባይነት እንዲያገኝ ምቹ ኹኔታን እንደፈጠረ ይገምታል፡፡ በተጨማሪም በኒክልስበርግ (እንዲኹም በሌሎች) ዘንድ መጽሐፈ ሄኖክ እንደ መጽሐፈ ጥንቆላ (Magical Book) እና አምልኮተ አጋንንትን (demonolatry) የሚያስተምር ተደርጎ ስለሚቄጠር በእነርሱ አመለካከት ኢትዮጵያ እስከ 5/6ኛው መ.ክ.ዘ.[18] በአምልኮ ጣዖትና በክፉዎች መናፍስት (evil spirits) ቁጥጥር ውስጥ እንደነበረች ስለሚያምኑ ለመጽሐፈ ሄኖክ በኢትዮጵያ የክብር ቦታ አግኝቶና ተጠብቆ ለመኖሩ እንደ ምክንያት ተወስዷል፡፡በመጨረሻም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መጽሐፈ ሄኖክን ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደ አንዱ አድርጋ የተቀበለችው እንደ አውሮፓውያን ሊቃውንት መጻሕፍትን መርምሮ ሃይማኖታዊ የኾኑትንና ያልኾኑትን ለይቶ ማወቅ የሚያስችል የትምህርተ ሃይማኖት ብቃት ስላልነበራት ነው በማለት ኒከልስበርግ ይደመድማል[19]፡፡

---

[18] አብዛኛዎቹ ምዕራባውያን አጥኚዎችና የእነርሱ ተጽዕኖ ያደረባቸው አንዳንድ የሀገር ውስጥ ጸሓፊዎች ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በ4ኛው መ.ክ.ዘ እንደኾነና ከዚያ ቀድሞ በነበረው ዘመን ግን ጣዖት ስታመልክ የኖረች አድርገው የሚጽፉ ሲኾን ኒከልስበርግ ደግሞ ይኸም አልበቃው ብሎ ክርስትና ከተቀበለች በኋላም እስከ 6ኛው መ.ክ.ዘ በመናፍስትና ጣዖት አምልኮ ውስጥ እንደ ነበረች ለመግለጽ ሞክሯል፡፡ ይኹን እንጂ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ምሁራን የሚያስረዱት ሀገሪቱ ቀድሞ በሕገ ልቡና ከዚያም በሕገ ኦሪት ስትመራ የኖረችና በኋላም በ34 ዓመተ ምሕረት የክርስትና ሃይማኖትን ተቀብላ በሐዲስ ኪዳን የምትመራ መኾኗን ሲኾን 4ኛው መ.ክ.ዘ ክርስትና የተጠናከረበትና መንግሥታዊ ሃይማኖት (State religion) ለመኾን የደረሰበት ዘመን እንደኾነ ያስረዳለሁ፡፡(Lule Melaku, Histroy of Ethiopian Orthodox Church (2008: 63).

[19] *the book's acceptance was affected by elements and conditions indigenous to Ethiopia and Ethiopian Christianity.... The story of the watchers' breeding a world of demons, which still prey on humanity, resonated in an environment where demons and spirits were part of one's understanding of everyday life. The book's developed angelology, with its plethora of heavenly intercessors and guardian spirits, was also compatible with such a worldview.*

*... The book's portrayal of angels binding evil spirits (10:4–5, 11) and the inclusion of a text like 69:4–5 were compatible with magical practice, and magic spells were in fact identified with Enochic revelation. 1 Enoch's focus on the created world, its sacred cosmology and geography and its flora and fauna, may have contributed to the book's popularity and helped it to exude a sense of familiarity. In a country of deep ravines and high mountain peaks—some of them sacred—the story of the watchers' descent onto Hermon (chap. 6) and the accounts of Enoch's journeys to the great mountain ranges of the west and east and the valleys of punishment would have led the reader's imagination through familiar terrain. Enoch's journeys through the spice orchards to the great tree of paradise would have resonated in a world where groves of trees were sacred. Many of the wild animals that preyed on the Israelite sheep that populate Enoch's second dream vision were part of the everyday experience of many Ethiopians....In short, 1 Enoch took root in Ethiopia because: (a) it was brought there by missionaries who came from an environment that had long cherished the book; (b) its worldview spoke to the Ethiopians' worldview, and the environment it imaginatively portrayed resonated with their environment; and (c) Ethiopian Christianity lacked the theological and intellectual counterforces that led to the book's rejection in Mediterranean Christianity.*

ኒከልስበርግ ምንም እንኳ መጽሐፈ ሄኖክን ለ50 ዓመታት ያክል በማጥናት(እርሱ እንደ ነገረን) ብዙ ትሩፋቶች ቢለግሰንም ከላይ ላስቀመጣቸው የተሳሳቱ መላምቶች ግን ሊተች ይገባዋል፡፡ የኒከልስበርግ መላምቶች አሳማኝነት የሚጎላቸውና ከጥያቄ ሊያመልጡ የማይችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እርሱ እንዳለው መጽሐፈ ሄኖክ ባንድ መልኩ ከጥንቆላና እኩያን መናፍስት ጋር የሚያያዝ ከኾነ በሌላ መልኩ ደግሞ መጽሐፉን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት የግብፅ ጳጳሳት ከኾኑ ጳጳሳቱ ሲያስተምሩና ሲያስፋፉ የኖሩት ጥንቆላንና ትምህርተ አጋንንትን ወይስ ትምህርተ ክርስቶስን? በተጨማሪም ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሺሕ ዓመት ጀምሮ በሕገ ኦሪት ስትመራ አግዚአብሔርን ስታመልክ የኖረች ሀገር መኾኗን የሚያስረዱ ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ እሴቶች ለምሳሌ፡- ግዝረት፣ሥርዓተ-ምግብ፣ ታቦት፣ መሥዋዕተ ኦሪት የተሰዋባቸው ቦታዎችና ቅዱሳት ንዋያት ወዘተ አማናዊ ምስክር ኾነው የሚገኙባትን ሀገር ከክርስቶስ ልደት በኋላም እስከ 6ኛው መ.ክ.ዘ ጣዖትን ስታመልክ የነበረች አድርጎ ማቅረብ ምን ያህል ተአማኒነት አለው?[20]ከኹሉምበላይ አንድ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊትና አስተምህሮ ጠንቅቆ የማያውቅ ጸሓፊ መጽሐፈ ሄኖክ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ በቂ የሃይማኖት ዕውቀት ስለሚያንሳት ወይንም ስለሌላት ነው ብሎ መገመትና መጻፍ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የተደረገ 'ምሁራዊ ትንኮሳ' (Intellectual harassment) ከመኾነ የዘለለ ትርጉም አይሰጥም፡፡ ምክንያቱም ፍረጃው መጽሐፉን ለዘመናት ሲያነቡት ሲተረጉሙት ሲማሩትና ለሌሎች ሲያስተምሩት የኖሩትን የቀደሙትንም ኾነ ያኹኑን ዘመን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለሚያካትት ነው፡፡ በመኾኑም የዚኽ ጥናት ዋና ዓላማ፡- መጽሐፈ ሄኖክ በመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ያለውን ቦታ ማሳየትና በይዘቱም እንደማጣቀሻ (Refference) እና ምንጭ (Source) ኾኖ ማገልገሉን በአብነት ማሳየት ነው፡፡

- በተጨማሪም ከመጽሐፈ ሄኖክ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ በሌሎች የብራና

[20] በታሪክ እንደሚታወቀው በንግሥተ-ሳባ እና በንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በቀዳማዊ ምኒልክ አማካኝነት ታቦተ ጽዮንን ጨምሮ 318 ሌዋውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል፤ መጻሐፍትንም ወደ ግዕዝ ተርጉመዋል (Tewodros Abraha and Seyfe Sillase Yohanns, as cited by Mersha Alehegn, *The Ethiopian Commentary on the Book of Genesis: Critical Edition and Translation.* Germany: Memminger MediemCentrum AG. (2011:2). እንዲኹም በአራቱ ማዕዘናተ ዓለም ያሉት አይሁዶች በዓልን ለማክበር በኢየሩሳሌም ይሰባበሱ እንደ ነበረ ኹሉ ኢትዮጵያውያንም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአንድ ሺህ ዓመት ተመሳሳይ ሃይማኖታዊ ጉዞ ያደርጉ የነበረ ለመኾኑ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 27 ላይ የተዘገበው የኢትዮጵያው ጃንደረባ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ በመሆኑም ከዚኽ ታሪካዊ ዳራ በመነሣት መጽሐ ሔኖክ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ወይንም ደግሞ ከዚያበኋላ ባለው አንድ ሺሕ ዘመን ውስጥ ያለማቋረጥ ወደ ኢየሩሳሌም ሲጓዙ በነበሩ ሃይማኖታዊ ተጓዦች ሊኾን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡

ጽሑፎች ውስጥ የተጠቀሱ ቃላትን፣ ሐረጋትን፣ ዐረፍተ ነገሮችን አንቀጾችን (paragraphs) ከተጠቀሱበት ዐውድ በመናሣት መጽሐፈ ሄኖክ በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት እንዴት ተነበበ? ወይንም ተተረጎመ? የሚለውን ማየትና መረዳት ነው።

- እንዲኹም የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የቅኔ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ለቅኔ ምሥጢር ማፍለቂያነት እንዴት እንደተጠቀሙበትና በመጽሐፈ ሄኖክ የተገለጠን ሐሳብ በቅኔያቸው እንዴት እንዳንጸባረቁት ማሳየት ነው።

- በመጨረሻም በሄኖካዊ የግዕዝ ጽሑፎች (Enochic Gə‘əz Literature s)[21] ውስጥ ያሉትን ምሥጢራዊ ትምህርቶች ፈልቅቆ ማውጣትና ከተለያዩ እይታዎች አንጻር ትንታኔ መስጠት ይኾናል።

ከላይ የተገለጸውን የዚኽን ጥናት ዐቢይና ንዑስ ዓላማዎች ግብ ለማድረስና የጥናቱን ተግባር በተገቢው መንገድ ለማስኬድ ይቻል ዘንድ ገላጪ የጥናትና ምርምር ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይኽ ዘዴ የተመረጠበት ዋና ምክንያት በልዩ ልዩ የጽሑፍ መዛግብት ላይ ተመርኩዞ ለሚካኼድ ጥናታዊ ሥራ ተስማሚ በመኾኑ ነው፡፡ ለዚኽ ጥናት ግብዓት የሚኾን መረጃ የተሰበሰበበት መንገድም ልዩ ልዩ ጥንታዊ የብራና ጽሑፎችን እና የትርጓሜ መጻሕፍትን በቀዳሚ የመረጃ ምንጭነት በመጠቀም ነው፡፡ በመኾኑም የዚኽ ጥናት ርእሰ ጉዳይ ከኾነው ከመጽሐፈ ሄኖክ ጋር በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ምንባባት በመውሰድ ከዋናው ምንጭ (መጽሐፈ ሄኖክ)ከየትኛው ምዕራፍና ቁጥር እንደተወሰዱና ለምን ዓላማ (ምን ለመግለጽ) እንዳገለገሉ ሰፊ ትንታኔ ቀርቧል፡፡

# ፪. የመጽሐፈ ሄኖክ አስተዋጽኦ (Role) በመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ

የመካከለኛው ዘመን የግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ እንደገና በከፍተኛ ደረጃ የተስፋፋበትና አያሌ መጻሕፍት የተጻፉበት ዘመን በመኾኑ “ወርቃማው የሥነ ጽሑፍ ዘመን” ይባላል። በዚኽ ዘመን የነበሩ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን ያነቡት፣ ያጠኑት፣ ይመረምሩትና ለድርሰቶቻቸው እንደ ምንጭ (Source) ይጠቀሙበት እንደ ነበር ለማወቅ የዘመኑን ድርሳናት መመርመር አስፈላጊ ነው። በመኾኑም መጽሐፈ ሄኖክ በልዩ ልዩ ብራናዎች ለምሳሌ በመጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምሥጢር፣መጽሐፈ ባሕርይ፣መጽሐፈ ስንክሳር፣ መጽሐፈ ፀሐይ፣መጽሐፈ ሰዓታት፣ድርሳነ ዑራኤል፣አርኬ፣ መልክአ ጉባኤ፣ ነግሥ እና

[21] ከመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅሶችን በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ ያካተቱ ጽሑፎች ሄኖካዊ ጽሑፎች ይባላሉ፡፡

በተለያዩ ቅኔዎች መጽሐፈ ሄኖክ በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ ተጠቅሶ እንደሚገኝ በዚኽ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚኽ አጭር ጽሑፍ ኹሉንም ማቅረብ ባይቻልም ለምሳሌ ያኽል ከብራናዎቹ የተወሰዱትን የሚከተሉትን ምንባባት እንመልከት፡፡

## ፭.፩. ሄኖክ በመጽሐፈ ብርሃን (EMML 7001)

መጽሐፈ ብርሃን በ15ኛው መ.ክ.ዘ በዓፄ ዘርዓያዕቆብ የተደረሰ ሲኾን ስያሜው እንደሚያመለክተው ብርሃን የተባለ ክርስቶስን ማእከል ያደረገና ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚያደርስ መኾኑን ጸሓፊው ይገልጻል::[22] ደራሲው ስለ መጽሐፈ ሔኖክ አስፈላጊነት በመግለጽ መጽሐፉን የሚነቅፉትን እንደሚከተለው ይሞግታል፡፡

*ወለመጽሐፈ ሄኖክሰ ንትዌከፎ በእንተ ዘዓቀምዎ ስምዓ ሐዋርያት እንዘ ይብሉ ዘከመ ተነበየ ሄኖክ ዘውእቱ ሳብእ እመነ አዳም...ጳውሎስኒ ይቤ፡- በተአምኖ አፍለሶ ለሄኖክ ከመ ኢይርአዮ ለሞት ወኢተክበ እምድኅረ አፍለሶ እግዚአብሔር፤ እምቅድመ ፍልሰቱ ሰማዕተ ኮኖ ከመ አሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሄር፡፡ ወእግዚአብሔርኒ ኮነ ስምዓ በእንቲአሁ በመጽሐፈ ኩፋሌ እንዘ ይብል ለሙሴ... ወውእቱ ቀዳሚ ጸሐፈ ስምዓ ለደቂቀ እስራኤል ውስተ ትዝምደ ሰብአ ምድር፤ ወሱባኤሆሙ ለኢዮቤልዩ ውእቱ ነገረ፤ ወመዋዕለ ዓመታት አይድዓ፤ ወዐውራኃተ ሠርዓ ወሰንበታተ ዓመታት፡፡ ወካዕበ እንዘ ያጸድቅ ነገሮ ለሄኖክ ይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ በመጽሐፈ ኩፋሌ ወአንተኒ አዝዞሙ ለደቂቀ እስራኤል ይዕቀቡ ዓመታተ በዝ ኍልቊ ፫፻ወ፷፬ (ሠለስቱ ምዕት ወስሳ ወረቡዓ) መዋዕለ*

[22] "...ሰመይናሁ ለዝንቱ ድርሳን መጽሐፈ ብርሃን ዘይምህር አምልኮቶ ለእግዚአብሔር ብርሃን...ዝንቱ ድርሳን ዘይሰመይ መጽሐፈ ብርሃን ዘበትርጓሜሁ መጽሐፈ ክርስቶስ ብርሃን እስመ ይመርሖሙ ለክርስቲያን ኀበ ርቱዓ አሚን ወያበጽሖሙ ለክርስቲያን ኃበ ክርስቶስ ብርሃን በከመ ለሊሁ በእንተ ርእሱ ይቤ አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ዘተለወኒ ኢየሐውር ውስተ ጽልመት.../ ይኽንን ድርሳን መጽሐፈ ብርሃን ብለን ሰየምነው፤ ብርሃን የተባለ እግዚአብሔርን ማምለክን ያስተምራልና፡፡ ይኽ መጽሐፈ ብርሃን የተባለ ድርሳን ትርጓሜው የብርሃን ክርስቶስ መጽሐፍ ነው፤ ክርስቲያኖችን ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ይመራቸዋል፤ ወደ ብርሃን ክርሰቶስ ያደርሳቸዋል፡፡ እርሱ
/ክርስቶስ ስለራሱ እንዲኽ እንዳለ የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፣የሚከተለኝ በጨለማ ውስጥ አይሄድም... ":

ትርጉም፡- የሄኖክን መጽሐፍ የምንቀበለው ሐዋርያት ምስክርነት ስላቆሙለት ነው፡፡ እንዲህ እያሉ፡፡ ከአዳም ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ እንደተናገረው ....፡፡ ጳውሎስም ተናግሯል፡፡ ሄኖክ ሞትን እንዳያየው በእምነት ሰወረው/አሳረገው፡፡ እግዚአብሔር ከሰወረው በኋላም አልተገኘም፡፡ ሄኖክ እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው ከመወሰዱ በፊት ምስክር ሆነው፡፡ እግዚአብሔርም ስለ እሱ ምስክር ሆነ፡፡ በመጽሐፈ ኩፋሌለሙሴ እንዲህ አለው.... በምድር ላይ በሰው ልጅ ዝምድና ለእሥራኤል ልጆች ምስክርነት አስቀድሞ የፃፈ እሱ ነው፡፡ የኢዮቤልዩ ሱባኤያቸውን የተናገረ እሱ ነው፡፡ የዓመታትን ጊዜ የተናገረ እሱ ነው፡፡ ወሮችን፣ የዓመታትን ሰንበቶች የሠራ እሱ ነው፡፡ ዳግመኛም የሄኖክን ነገር እውነት ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር በመጽሐፈ ኩፋሌ ሙሴን አለው፡፡ አንተም የእሥራኤልን ልጆች አዘዛቸው በዚህ በ፫፻፷፬ (364) ቁጥር ዓመታትን ይጠብቁ

*ወይከውን ፍጹመ ዓመተ (cf En 74:9-13)።*

*ርኢኬ ዘይብል ኢይትዌከፎ ለመጽሐፈ ሄኖክ ሶበ ታቀውም ሊተ ስምዓ ለዘዓቀምዎ ሐዋርያት ስምዓ በመጽሐፈ መልእክቱ ለይሁዳ እኁሁ ለያዕቆብ። ወእግዚአብሔርኒ ኮኖ ስምዓ ለመጽሐፈ ሄኖክ ወነገሮ ለሙሴ ኍልቈ መዋዕለ ዓመት። እፎኑ ይትከሀለክ ታእምር ዑደተ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት፤ ምልዓተ ብርሃን ወሑፃጼሁ፤ ወሥርዓተ ዓመታት ዘእንበለ ሄኖክ ። ወሐዋርያትኒ ይቤሉ በእንተ ክብረ ሄኖክ... ወእምሰ አክበርዎ ወአስተዓረይዎ ሐዋርያት በዲድስቅልያሆሙ ለመጽሐፈ ሄኖክ ምስለ መጽሐፈ ሙሴ ወኢሳይያስ ወዳዊት ወመጻሕፍተ ካልዓን አበው ቀደምት እስመ እሙንቱ ነቢያቲሁ ለእግዚአብሔር፤ በከመ ይቤሉ ሐዋርያት በዲድስቅልያሆሙ እስመ አበው ቀደምት ጥዩቅ እምንቱ አፉሁ ለእግዚአብሔር፤ ወሄኖክኒ ነቢይ እምአበው ቀደምት ውእቱኒ አፉሁ ለእግዚአብሔር። ወበእንተዝ ናፈቅሮ ወንትዌከፎ ለመጽሐፈ ሄኖክ አእሚረነ ከመ ተወክፍዎ ሐዋርያት ለስምዕ...(ff 81-83)።*

*ትርጉም፡- ተመልከት! የሄኖክን መጽሐፍ አልቀበልም የሚለውን "ሶበ ታቀውም ሊተ ስምዓ" ሐዋርያት በያዕቆብ ወንድም በይሁዳ መጽሐፈ መልእክት ምስክርነትን ላቈሙለት እግዚአብሔርም ለሄኖክ መጽሐፍ ምስክር ሆኗል። ለሙሴም የዓመታትን የጊዜ ቍጥር ነግሮታል። የፀሐይን፣ የጨረቃን እና የከዋክብትን ዙረት (ዑደት)፣ የብርሃንን መሙላት እና መጉደል፤ የዓመታትን ሥርዓት ያለ ሄኖክ ታውቅ ዘንድ እንዴት ይቻልሀል?ሐዋርያት ስለ ሄኖክ ክብር ይናገራሉ።.... ሐዋርያት በዲድስቅሊያቸው የሄኖክን መጽሐፍ ከሙሴ መጽሐፍ፣ ከዳዊት መጽሐፍ፣ ከኢሳይያስ መጽሐፍ እና የእግዚአብሔር ነብያት ተብለው ከሚጠሩ ሌሎች ቀደምት አባቶች መጽሐፍ ጋር ከአስተ ካከሉት እና ከአከበሩት፤ ሐዋርያትም በዲድስቅሊያቸው እንዳሉት የቀደሙ አባቶች የእግዚአብሔር አፍ (አንደበት) እንደሆኑ የታወቀ የተረዳ ነው። ሄኖክም እንደቀደሙት አባቶች ነብይ ነው። እሱም የእግዚአብሔር አፍ (አንደበት) ነው። ስለዚህ ሐዋርያት የሄኖክን መጽሐፍ ለምስክርነት እንደተቀበሉት አውቀን እንወደዋለን እንቀበለዋለን።*

ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፈ ሄኖክን መቀበል እንደሚገባ በአመክንዮ ያስረዳል። ሐዋርያት በትምህርታቸው ለምስክርነት (ለማስረጃነት) የጠቀሱት መኾኑን ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ (ቁጥር 14-15) “ዘከመ ተነበየ ሄኖክ ዘውእቱ ሳብእ እም አዳም...” ያለውን በዋቢነት ጽፏል። የነቢዩ ሄኖክንም የሃይማኖቱን ጽናት የምግባሩን ቅናት ለማስረዳት ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክት (ዕብ. 11:5) በመጥቀስ ዘርዓ ያዕቆብ ያትታል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሄኖክ የገለጠውን ስለ ቀናት፣ ወራት፣ ዓመታት ሰንበታት (ሱባኤያት) እና ኢዮቤልዩ አቆጣጠር በኋላም ለሙሴ በድጋሜ በመጽሐፈ ኩፋሌ እንዲጽፈው ማዘዙ

የመጽሐፈ ሄኖክን አስፈላጊነት የሚመሰክር መኾኑን ዘርዓ ያዕቆብ ጽፏል፡፡ ሐዋርያት በመልእክታቸውና ዲድስቅልያ በተባለው መጽሐፋቸው ስለ መጽሐፈ ሄኖክ የሰጡትን ምስክርነት የማይቀበልን ሰው "እፎኑ ይትከሀለከ ታእምር ዑደተ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋክብት፤ ምልዓተ ብርሃን ወሑፃዌሁ፤ ወሥርዓተ ዓመታት ዘእንበለ ሄኖክ.../ የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብትን ዑደት (መመላለስ) እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? የብርሃንን መሙላትና መጉደል፣ የዓመታትን ሥርዓት (አቆጣጠር) ያለ መጽሐፈ ሄኖክ እንዴት ማወቅ ትችላለህ?..." በማለት ደራሲው ይሞግታል፡፡ በመጨረሻም ሐዋርያት መጽሐፈ ሄኖክን ከሙሴ፣ ከኢሳይያስ፣ ከዳዊት ከሌሎቹም የቀደሙ አባቶች መጻሕፍት ጋር እኩል አድርገው ከቆጠሩት፣እኛም እንወደዋለን፤ እንቀበለዋለን፤ በማለት ይደመድማል፡፡

## ፳.፪. ሄኖክ በመጽሐፈ ሙላድ (Call No. 6838)

ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ክርስቶስ ልደት በሚያትተው በመጽሐፈ ሙላድ ድርሰቱ መጽሐፈ ሄኖክን ማጣቀሻ አድርጎ ተጠቅሞበታል፡፡ የትኛውንም ሃይማኖት የሚከተል ሰው ክርስቲያንም ይኹን አይሁዳዊ መጽሐፈ ሄኖክን ማቃለል እንደማይችል ከታች ያለው አንቀጽ ያስረዳል፡፡

*ስማዕ ኦ ብእሲ እመኒ ኮንከ ክርስቲያናዌ ወእመኒ ኮንከ አይሁዳዌ ወኢይትከሀለከ ትትከሐዶ ለሄኖክ እስመ ውእቱ ቀደመ ተነብዮ ወእምኵሉ እለ እምዓለም ነቢያት፡፡ ወእምኵሎሙ እለ ተነበዩ ልደቶ ለክርስቶስ እማርያም ድንግል በክልኤ፡፡ ወዓዲ ጥምቀቶ...፡፡ እስመ ሄኖክ ርእየ ሙፃኣ ፀሐይ ወምዕራብ ፀሐይ ዘከመ ይሠርቅ ወየዐርብ ለለወርኁ ወለለ ዕለቱ በመሳክወ ሰማይ፡፡ በከመ ይቤ ለሊሁ:- ወሕጸራ ለዕለት ወለሌሊት ወኑኃ ለዕለት ወለሌሊት በምሕዋረ ፀሐይ ውእቱ ይትሌለይ፡፡*

ትርጉም፡- ሰው ሆይ ስማ! ክርስቲያን ብትሆንም አይሁድ ብትሆንም ሄኖክን ትክደው ዘንድ አይቻልህም፡፡ እሱ በዓለም ውስጥ ከነበሩ ነብያት ሁሉ፤ በኹለት ወገን ድንግል ከሆነች ከማርያም የክርስቶስን መወለድ ከተናገሩት ነብያትም ሁሉ በፊት አስቀድሞ ትንቢትን ተናግሯል፡፡ ጥምቀቱንም እንዲሁ....፡፡ ሄኖክ የፀሐይን መውጫና መግቢያ፤ ፀሐይ በየወሩ እና በየእለቱ ሲወጣና ሲገባ በሰማይ መስኮት ተመልክቷል (አይቷል) እና፡፡ እሱም እንዳለው፡- የቀኑ እና የሌሊቱ ማጠር፤ የቀኑ እና የሌሊቱ መርዘም የሚለየው (የሚታወቀው) በፀሐይ መንገድ ነው፡፡

*ወበእንቲአሁ ይነውሕ ምሕዋሪሁ ዕለት እምዕለት ወሌሊት እምሌሊት (cf. 1En.72: 33-35)፡፡ እስመ ለፀሐይ ብዙኅ ውእቱ ኅቡአቲሁ፡፡ ወለውሉደ ምድርኒ ሄኖክ*

*ነገረ ወምሥጢራቲሃ ወሕፀፂሃ (ለወርኅ)... ወካዕበ ይቤ ሄኖክ በእንቲአሃ:- "ወበኆኅት ቀዳማዊ በመዋዕል ምዕት ወሰብዓ ወሰብዓቱ ወዘመነ ዚአሁ ሙፃኡ ሠለስተ ወርኃ ያስተርኢ በበሰላሳ። ወሠለስተ ወርኃ ያስተርኢ በበዕሥራ ወተሱዕ መዋዕል:: በሌሊት ያስተርኢ በበዕሥራ ከመ ብእሲ ወመዐልተ ከመ ሰማይ እስመ ካልዕ ምንትኒ ኣልባቲ ዘእንበለ ብርሃነ ዚኣሃ" (cf. 1En. 78:15-17)። ወካዕበ አርአየ (ርእየ) ሄኖክ ሥርአታቲሆሙ ለከዋክብት እለ የዐርቡ መካናቲሆሙ ወአዝማኒሆሙ ወበዓላቲሆሙ ወበአውራኃቲሆሙ። ወለከዋክብተ ጽባሕሂ ወለከዋክብተ ምሴት አእመረ ኅቡረ ምስሌሆሙ (cf. 1En. 82:9-11) ። ኦ ብእሲ መስተካሕድ እሉንተ ሶበ ትፈክር ትሰመይኬ ጠቢበ ወማእምረ። ስማዕ ኦ ብእሲ ዘትትከሓዶ (ዘትክሕዶ) ለሄኖክ እምአይኑ ታመጽእ ዕለታተ ሠለስተ ምእተ ወስሳ ወአርባዕተ ዕለታተ። ወዓዲ አውራኃ ዐሠርተ ወክልኤተ። ወዓዲ ካዕበ ሰብዓ ምእተ ዓመታተ ዘውእቱ ሰባቱ ስሕ ዓመታቲሁ ለእግዚአብሔር። በከመ ነገረ ሄኖክ እንዘ ይብል ከመዝ:- "ወእምድኅረ ዝንቱ በሰንበት ዐሥርት ሳብዒት ዕዳ ባቲ ኵነኔ እንተ ለዓለም ዓቢይ ዘይትቤቀል እማእከሎሙ መላእክተ ወሰማይ ቀዳማዊ ይወጽእ ወየሐልፍ። ወሰማይ ሐዲስ ይትረአይ። ወኵሎሙ ኃይለ ሰማያት ያበርሁ ለዓለም ሰብዓተ ምክዕቢተ። ወእምድኅረዝ ሰንበታት ብዙኃት እለ አልቦን ኍልቍ በዓለም በኂሩት ወበጽድቅ ይከውኑ..."(cf. 1En. 91:15-17)። ወአንተሰ አይሁዳዊ ትብልአ ከመዝ ወእምድኅረ ሰብዓቱ ሲህ ዓመታት ሀሎ ዓመታት ብዙኅ። ዘንተ ዘትትናገር ሶበ ተኃጥእ እድሜሁ ወውሳኔሁ ለትፍሥሕትከ ወሐሜትከ እስመ መዝበረ ወኃመደ ኮንከ...። (ff 4s-47) ስማዕ ኦ ብእሲ ክርስቲያናዊ ጠቢብ፣ በስመ ሥላሴ ዕቱብ፣ ልደትከኒ ክዑብ፣ አእምሮ ሃይማኖትከ ዕድው እምአብዳነ ልብ። እመሂ መጽአ ብእሲ እምሥራቅ ወእምእራብ፣ እምሰሜን ወእምደቡብ፣ወእምኵሉ ትርብዕተ ዓለም ርኂብ፣ እመሂ ጾሙ ወእመሂ ፋሲካሁ ወእመሂ በዓላቲሁ፣እመሂ በጸሐይ ወእመሂ በወርኅ ወእመሂ በኮከብ፣ዘእንበለ ሄኖክ ኢይትከሃል ኵሉ ሐሳብ። ( f 165)*

*ትርጉም፡- በእሱም የእለት ከእለት የሌሊትም ከሌሊት ጉዳናው ይረዝማል (cf.1En.72: 33-35)። የፀሐይ መሠወሪያው ብዙ ነው እና። ሄኖክ ለምድር ልጆች የጨረቃን ምስጢሮቿን፣ ጉደለቶቿን ተናገረ። ዳግመኛ ሄኖክ ስለእሷ እንዲህ አለ በመጀመሪያው ደጃፍ (በር) በ፫፻፷፬ ዘመን በራሱ ዘመን መውጫው ለሦስት ወሮች በ፴ በ፴ ይታያል። ለሦስት ወሮችም በ፳፱ በ፳፱ ይታያል። ሌሊት በ፳ በ፳ እንደ ሰው ይታያል። ቀን ደግሞ ሰማይ መስሎ ይታያል። ከእራሷ ብርሃን ሌላ ምንም ብርሃን የላትም እና። (cf. 1En. 78:15-17) ። ዳግመኛም ሄኖክ የከዋክብትን የሚገቡበትን ቦታ፣ የዘመናቸውን፣ የበዓላቶቻቸውን እና የወሮቻቸውን ሥርዓት አየ። የንጋት ኮከቦችን፣ የምሽት ኮከቦችን በአንድነት ከእነሱ ጋር አወቀ ( )። የምትክድ አንተ ሰው ሆይ! እነዚህን በተረጎምህ ጊዜ አዋቂ እና ጥበበኛ ትባላለህ። ሄኖክን የምትክደው አንተ ሰው ሆይ ስማ! ፫፻፷፬*

*(364) እለታትን ከየት ታመጣለህ? ዳግመኛም ፲፪ (12) ወሮችን፣ ሰብአ መቶ (፸፻) ዓመታትን እነሱም የእግዚአብሔር ሰባት ሺሕ ዓመታትን ከየት ታመጣለህ? ሄኖክ እንዲህ ብሎ እንደተናገረ ከዚህ በኋላ በሰባት ሺህኛውን ሰንበት እዳ አለባት መላእክትን ከመካከላቸው ለዘለዓለም የሚበቀል ታላቅ ኩነኔ አለባት። የመጀመሪያው ሰማይ ይወጣል ያልፋልም። አዲስ ሰማይ ይታያል ሁሉም የሰማያት ኃይሎች እጥፍ ይበራሉ። ከዚህ በኋላ ቍጥር የሌላቸው ብዙ ሰንበቶች በቸርነት እና በእውነት በዓለም ይሆናሉ። አንተ አይሁዳዊ እንዲህ ትላለህን? ከሰባቱ ሺህ ዓመቶች በኋላ ብዙ ዓመት አለ። ይህን ስትናገር የተድላ ደስታህን እድሜውን እና ውሳኔውን ባጣኸው ጊዜ አመድ እና ትቢያ ትሆናለህ እና (ff 4s-47)። በሥላሴ ሥም የተባረክህ፣ ሁለት ልደት ያለህ የሃይማኖት ማስተዋልህ ከሰነፎች ልብ ያለፈ አንተ ጥበበኛ ክርስቲያን ሰው ሆይ ስማ! ሰው ከምሥራቅም ኾነ ከምእራብ፣ ከሰሜንም ኾነ ከደቡብ ሰፈ ከሆነችው ዓለም ከአራቱም አቅጣጫ ቢመጣ፣ ጾሙም፣ ፋሲካውም፣ በዓላቶቹም ቢኾን፣ በፀሐይም፣ በጨረቃም፣ በከዋክብትም ቢኾን ኹሉም ሐሳብ ያለ ሄኖክ አይቻልም (f165)።*

በዚኽ አንቀጽ ዘርዓ ያዕቆብ የክርስቶስን ልደት፣ ጥምቀት… አስቀድመው ከተናሩ ነቢያት ቀዳሚው ሄኖክ መኾኑን ይጠቅሳል። የፀሐይን መውጫና መግቢያ፣በየዕለቱና በየወሩ ፀሐይ የሚወጣበትንና የሚገባበትን መስኮቶች፤የያንዳንዱ ቀንና ሌሊት መርዘምና ማጠር የሚለየው በፀሐይ መኾኑን እንዲኹም የፀሐይ መግቢያና መውጫው ብዙ መኾኑን (12 መስኮቶች እንዳሉት)፤የጨረቃንም ምሥጢር (እንዴት እንደሚወጣና እንደሚገባ፣ እንደሚጎልና እንደሚሞላ፣ብርሃኑን ከፀሐይ እንዴት እንደሚቀበል፣በቀንና በሌሊት ለሰው ልጆች እንዴት እንደሚታይ …)፤ የከዋክብትንም ሥርዓት የሚታዩበትን ወራት፣በዓላትና ዘመናት… ስለሚያስረዳ መጽሐፈ ሄኖክን ማንኛውም ሰው ከምሥራቅም ይኹን ከምዕራብ ከደቡብም ይምጣ ከሰሜን ሊቀበለው እንደሚገባ ዘርዓ ያዕቆብ ይሞግታል። የትኛውንም ሃይማኖት የሚከተል ስው፣ በፀሐይ በጨረቃም ይኹን በከዋክብት ዘመናትን ቢቆጥር፣ ጾሙና ፋሲካው በዓላቱ የሚውሉበትን ቀናት ለይቶ ለማወቅ መጽሐፈ ሄኖክ አስፈላጊ መኹኑን ደራሲው ያስረዳል።

## ፭.፫.ሄኖክ በመጽሐፈ ባሕርይ (Call No. EMML1480)

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዚኽኛው ድርሰቱ መጽሐፈ ሄኖክን በስፋት የጠቀሰው ሲኾን ለምሳሌ ከዚኽ በታች በቀረበው አንቀጽ ጠንቋዮችንና ጥንቆላቸውን ሲቃወምበት እናነባለን።

*… ወአንትሙሰ ክርስቲያን ኢትስምዕዎ ለጠንቋሊ…እሉ እሙንቱ ጠንቋልያን ዘይቤልዎሙ ሐዋርያት በሲኖዶሶሙ አይሑድ ወመጣዐውያን ደቂቀ ትምህርቶሙ*

*ለመላእክተ ጽልመት እኩያን እለ ኀደጉ ሰማየ ልዑለ ወምቅዋመ ቅዱሰ (cf. En12:4, 15:3)፤ ወአብደሩ ከመ ያማስኑ በኵሉ ርኵሰ ዚአሆን(ሙ) ለአንስት። ወመሀሩ ለውሉደ ሰብእ ሩጻተ ፀሐይ ወወርኀ ወከዋክብት ወኵሎ ምራያተ፤ ወኵሎ ምግባራተ ምኑናተ(cf. En8:1-4)። ያድኀነነ እግዚአብሔር እመክፈልቶሙ ለእሉ ለነ ለሕዝቡ ለአባግዐ መሬቱ፤ ወይረስየነ ናምልኮ በጽድቅ ወበርትዕ ሎቱ ለባሕቲቱ ለዓለመ ዓለም አሜን (f 57)...።*

ትርጉም፡- እናንተ ክርስቲያኖች ጠንቋይ አትስሙ።... እነዚህን ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው ጠንቋይ አይሁድ፣ ምትሐተኞች፣ የተቀደሰውን መቋሚያ ሰማይ ልዑልን የተው ክፉ የኾኑ የመላእክተ ጽልመት የትምህርት ልጆች ይሏቸዋል። በሴቶቻቸው ርኩሰት ሁሉ ለማጥፋት ይቀዳደማሉ። ለሰው ልጆች የፀሐይን፣ የጨረቃን፣ የከዋክብትን ሩጫ፣ ምትሐትን ኹሉ፣ የተናቁ ምግባራትን ኹሉ ያስተምራሉ። እግዚአብሔር እኛንም መንጋውንም ከእነሱ እጣ ፈንታ ያድነን። በእውነት እና በቅንነት እንድናመልከው ያድርገን ለእሱ ለብቻው ለዓለም ዓለም አሜን።

*....ወአንተኒ አ ብእሲ ዘተሰመይከ ክርስቲያናዌ፤ ወእምነ ክርስቲያን ዘተሠየምከ መዘምረ፤ ... ወእምነ ጳጳስ ዘተሠየምከ ሊቀ ጳጳሳተ፤ አልቦኬ ዘየዓቢ እምዝ መዐርገ ክህነት... ወአንተሰ እምድኅረ በጻሕከ ውስተ ዝንቱ መዐርግ ክቡር አንሐልከ ኩሎ መዐርገ ክህነት፤ ወኮንከ ዕሩቀ እምጥምቀተ ክርስትናከ። ወረሰይከ ርእሰከ አይሁዳዌ ወመጠዐዌ በኀርየትከ ዕለተ እምዕለት፣ ወሰዐተ እምሰዐት፤ ወበነጸሮትከ ፀሐየ ወወርኀ ወከዋክብተ በትእምርተ እኪይ በትምህርቶሙ ለመላእክተ ጽልመት እለ ወድቁ እምሰማይ ዲበ ምድር፤ ወመሀሩ ርእየተ ከዋክብት ወኵሎ ትእምርታተ እኪይ። እሉ እሙንቱ በረቅያል ወኮከብኤል ወጣምኤል ወአስድረኤል አበወ ረአይት እለ ኮኑ ለከኒ አበው። በከመ ይቤ ሄኖክ ሳብዕ እምአዳም በረቅኤል መሀረ ረአይያነ ኮከብ፤ ወኮከብኤል ትእምርታተ፤ ወጠምኤል መሀረ ራእየ ኮክብ፤ ወአስድረኤል መሀረ ሩጻተ ወርኀ ለአኀጕሎተ ሰብእ....(ff. 57-58) , (cf. En8:1-4)*

*ትርጉም፡- አንተም ጥበበኛ ክርስቲያን ሰው ሆይ! ከክርስቲያንም ዘማሪ የተባልክ፣ ... ከጳጳሳትም ሊቀ ጳጳስ ተብለህ የምትጠራ ከዚህ የሚበልጥ የክህነት ማዕረግ የለም። አንተ ግን ከዚህ የከበረ የክህነት ማዕረግ ከደረስክ በኋላ ኹሉንም የክህነት ማዕረግ አፈረስክ። ከክርስትና ጥምቀትህም የተራቆትህ ኾንህ። ከሰዓት ወደ ሰዓት፣ ከእለት ወደ እለት በእራስህ ምርጫ እራስህን መጣዌ እና አይሁዳዊ አደረግሀ፣ ፀሐይን፣ ጨረቃን እና ከዋክብትን የምታየው ከሰማይ ወደ ምድር በወደቁ የጨለማ መልእክተኞች ትምህርት በክፉ ምልክት ነው። ኮከብ ማይትን እና ኹሉንም የክፋት ምልክቶችን አስተማረ። እነሱም ብርቅያል፣ ኮከብኤል፣ ወጣምኤል፣ አስድረኤል የረአይት አባቶች ናቸው። ለአንተም አባቶችህ ኾኑ ከአዳም ሰባተኛ የኾነው ሄኖክ እንዳለው ብርቅኤል ኮከብ ማየትን አስተማረ፣*

*ኮከብኤልም ምልክቶችን፣ ወጣምኤል ኮከብ መቁጠርን አስተማረ፤ አስረድኤልም ሰውን ለማጥፋት የጨረቃን ሩጫ አስተማረ።*

ከገጸ ምንባቡ እንደምንረዳው ዘርዓ ያዕቆብ ክርስቲያኖች ኹሉ ጠንቋዮችን እንዳይከተሉ ያሳስባል። እነዚኽም ጠንቋዮች የተቀደሰውንና ከፍ ያለውን መኖሪያቸውን የተዉ የክፉዎችና የጨለማ መላእክትን ትምህርት የሚከተሉ ናቸው። በሄኖክ እንደተገለጸው መላእክተ ጽልመት የተባሉትም ልዩ ልዩ ርኩሰትን፣ በፀሐይ በጨረቃ፣ በከዋክብት ማምለክንና ማሟረትን ያስተማሩ ናቸው። በመኾኑም ማንኛውም ክርስቲያን በልዩ ልዩ ማዕርግ የሚገኝ (መዘምር፣ አናጉንስጢስ፣ንፍቅ-ዲያቆን፣ሥረይ ዲያቆን፣ቄስ፣ኤጲስቆጶስ፣ጳጳስ፣ሊቀ ጳጳስ)[23] ጠንቋዮችን በመተባበር፣ ትምህርታቸውን በመስማትና ግብራቸውን በመከተል ከክርስቲያናዊ ሕይወት እንዳይራቆት ደራሲው ያስጠነቅቃል። ይኽም የሚያስረዳው በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከጨለማው መላእክት የመነጨው ልዩ ልዩ የጥንቆላ ትምህርትና ሥራ ምን ያኽል ተስፋፍቶ እንደ ነበርና በከፍተኛ ማዕርገ ክህነት ያሉትንም እንዳጠቃ "...ወአንተሰ እምድኅረ በጻሕከ ውስተ ዝንቱ መዐርግ ክቡር አንሐልከ ኹሎ መዐርገ ክህነት..." የሚለው ኀይለ ቃል በግልጽ ያሳያል። በመጨረሻው አንቀጽ የጨለማው መላእክት ስማቸው ከነ ግብራቸው መጠቀሱ ደራሲው ስለመጽሐፈ ሄኖክ ያለውን ጥልቅ ግንዛቤ ያስረዳል።

## ፭.፩.ሄኖክ በመጽሐፈ ምሥጢር (EMML 6456)

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽሐፈ ሄኖክን በድርሰቱ የተለያዩ ሐሳቦችን ለመግለጽ በተደጋጋሚ በቀጥታም ይኹን በተዘዋዋሪ የጠቀሰው ሲኾን ለምሳሌ ገነት በምሥራቅ በኩል በምድር ላይ ከፍ ብላ የምትገኝ መኾኗን ለማስረዳት መጽሐፈ ሄኖክን አስረጅ በማድረግ እንደሚከተለው ጽፏል።

*...ወቦ እለ ይቤሉ ከመ ገነትኒ ኤዶም ውስተ ሰማይ ይእቲ ወአኮ ውስተ ምድር። ወእመሰ በሰማያት ይእቲ ለምንትኬ ትቤ ቅድስት ኦሪት ወፈለግ ይወፅእ እምነ ቅድሜሃ ከመ ይስቅያ ለገነት ወእምህየ ይትፈለጥ ለአርባዕቱ መዓዝነ ዓለም...ወሶበሰ በሰማያት ይእቲ እምይቤ ይረድ ከመ ዘእምላዕሉ ወኢይቤ ይወፅእ እምገነት...። ወምድርሰ ዘነበረ አዳም ውስቴታ ጥቃ ገነት ይእቲ ዘአንጻረ ጽባሕ...። ወእምአዳም እስከ ኖኅ ነበሩ ደቂቀ አዳም ውስተ ጥቃ ገነት። ወሶበ አማሰኑ ውሉደ ሰብእ ፍኖቶሙ በዐሊወ ትእዛዛቲሁ ለእግዚአብሔር አመ ርደቶሙ ለትጉኃነ ሰማይ እለ ተደመሩ ምስለ አዋልደ ሰብእ ወመሀሩ መቲረ ዐሥራው ወገቢረ ሥራይ ወርእየተ ኮከብ ወመልአተ ምድር ዐመፃ ወትዕቢተ*

[23] እነዚህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የአገልግሎት ደረጃዎች ናቸው።

*ወትእግልተ ፍግዓ ወዝሙተ ወቀትለ ወክዕወተ ደም (cf. En7:1-5)። ወነስሐ እግዚአብሔር በእንተ ዘገብሮ ለእጓለ እመሕያው ወይቤሎ ለኖኅ ግበር ለከ መስቀረ በዘትድኅን አንተ...። ወገነትሰ ይእቲ ዘተካላ እግዚአብሔር ወይእቲ ትነብር ድሉተ ለርስተ ቅዱሳን ጽጌሃ ኢይትነገፍ ወፍሬሃ ኢየዐብር ወቈጽላ ኢይጸመሂ (cf. En24:4) እስመ እግዚአብሔር ተከላ...(ገጽ 84-89)።*

*ትርጉም፡- .... ገነት በምድር ሳይኾን በሰማይ ናት የሚሉ አሉ። ገነት በሰማይ ከኾነች ቅድስት ኦሪት ሰለሞን እንደዚኽ አለች፤ ወንዝ ከፊቷ ይወጣል ገነትንም ያጣታል። በዚኽም ዐራቱ የዓለም አቅጣጫዎች ይለዩበታል። ገነት በሰማይ ብትኾን ኖሮ ከላዩ ይወርዳል ባለ ነበር፤ ከገነትም ይወጣል አይልም ነበር።... አዳም በውስጧ የነበረባት ምድር በስተምስራቅ በኩል ከገነት አጠገብ ነበረች ከአዳም እስከ ኖኅ የነበሩ የአዳም ልጆች በገነት አጠገብ ኑረዋል የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣስ መንገዳቸውን ባጠፉ ጊዜ፣ የሰማይ ትጉሀን ወርደው ከሰው ልጆች ጋር በተቀላቀሉ ጊዜ፣ ሥር መበጠስን፣ ኮከብ መቁጠርን፣ ሥራይ ማድረግን አስተማሩ። ምድርም አመፃን፣ትእቢትን፣ መዳራትን፣ ዝሙትን፣ ግድያንና ደም መፋሰስን ተሞላች። እግዚአብሔርም ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ። ኖኅንም የምትድንበትን ታቦት ሥራ አለው። እግዚአብሔር የተከላት ገነትስ ይህች ናት። እሷም ለቅዱሳን እርስት ተዘጋጅታ ትኖራለች። አበባዎቿ አይረግፉም፤ ፍሬዎቿም አይጨማተሩም፣ ቅጠሎቿም አይጠወልጉም እግዚአብሔር ተክሏታልእና...*

አባ ጊዮርጊስ ገነት በምድር ላይ እንደምትገኝ ለመግለጽ ከአዳም እስከ ኖኅ ያሉት አባቶች በገነት አቅራቢያ መኖራቸውን ይገልጻል[24]። ይኹን እንጂ ትጉኃን የተባሉ ደቂቀ ሴት ከሰማይ (ከደብር ቅዱስ) በወረዱና ውሉደ ሰብእ (የሰው ልጆች) ተብለው ከተገለጹት ከደቂቀ ቃየል ጋር በተገናኙ ጊዜ ሥር መበጠስ፣ ኮከብ መቁጠርና ሥራይ ማድረግን በማስተማራቸው የሰው ልጆች በመንገዳቸው ኹሉ እግዚአብሔርን በደሉ። ምድር በዐመፃ፣ በቅሚያ፣በዝሙት፣በመገዳደልና ደም በማፍሰስ ተሞላች። ይኽም ፈጣሪን ስላስቀየመው በጉን የጠበቀ ኖኅንና ቤተሰቦቹን በመርከብ ሰውሮ ምድርንና በምድር ያሉትን በጥፋት ውኃ ቀጣቸው። እግዚአብሔር አስቀድሞ ለቅዱሳን ርስት ትኾን ዘንድ ያዘጋጃት ገነት የምድር ክፍል ብትኾንም ማየ አይኅ በምድር ላይ ሲዘንብ ልምላሜዋ ሳይደርቅ፣ቅጠሉዋ ሳይጠወልግ፣ ፍሬዋ ሳይረግፍ ተጠብቃ መኖሯን ሄኖክን ዋቢ በማድረግ አባ ጊዮርጊስ ያስረዳል።

[24] አዳም ከሞተ በኋላ ነገደ ሴትና ነገደ ቃየል ለኹለት እንደተከፈሉ፣ሴትም ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን በደብር ቅዱስ (አዳም ከገነት ሲባረር ያረፈበት ቦታ) ቃየልም ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ከደብር ቅዱስ በታች በሚገኝ ቦታ እንዳስቀመጣቸው በመጽሐፈ ቀሌምንጦስ ተጠቅሷል (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ገጽ 25)።

# ፩.፩.ሄኖክ በመጽሐፈ ሰዓታት (Call No. EMML7020)

አባ ጊዮርጊስ ከብሉይና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እየጠቀሰ ክርስቲያኖች የሌሊትና የቀን በማለት በኹለት ከፍለው የሚጸልዩትን የ መጽሐፈ ሰዓታት የጸሎት መጽሐፍ ሲያዘጋጅ መጽሐፈ ሄኖክንም እንደ እንድ ምንጭ ተጠቅሞታል። ለማስረጃ ያክል የሚከተለውን አንቀጽ ማየት በቂ ነው።

*…በምክረ ጥበብ (cf. En42:1) ተተክለ ሕሊናሆሙ ለከዋክብት ዘምስለ ሠርቅ ወዐረብ በበጊዜሁ ወለለአዝማኑ ወለለ አውራኂሁ (cf. En82:9) ፤ ወዑደታተ ፀሐይኒ ዘምስለ አብሀርቲሁ (cf.*

*… የከዋክብት ሕሊናቸው በየጊዜው፣ በየዘመኑ፣ በየወራቶቹ ከመውጫ እና መግቢያው ጋር የፀሐይም ዙረቶች (ዑደታት) ከብርሃኖቹ ጋር በምክር ጥበብ ተተከለ።*

*En72:4-37) ፤ ወናጸተ ወርኅኒ ለለመዋዕሊሁ ሎጻጼሁኒ እስከ ይተርፍ በከመ ዐውዱ (cf. En78:8)። ወልደ ብርሃኑኒ እንዘ ይትዌሰክ እምዕለት ዕለት እስከ ይመልእ ጥንቁቀ (cf. En73:8, 78:10)። ወኵሉ ሥሩዕ ወግቡር በኃይለ ሥላሴ ቅድስት…(f. 3)*

*…ዝ ውእቱ መልአክ ዘይቀጽብ ነፍሳተ ውስተ አኀጉሎቱ፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘይሜህር ሐሰተ እምዚአሁ፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘመሀሮ ለቃየል ይቅትል እኁሁ (cf. En69:6)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘሜጠ ሕሊናሆሙ ለውሉደ ሰማይ ከመ ይዘምዉ በአዋልደ ሰብእ እስከ አውለዱ ደመ ሥጋ (cf. En6:1, 69:4)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘረሰዮሙ ለረአይት ከመ ይቅትሉ ሰብአ ወከመ ያብዝኑ ሥራያተ ዲበ ምድር ወ (ሰገላ) በአዕዋፍ (cf. En7:4-5)፤ ዝ ውእቱ መልአክ ዘረሰዮ ለአፍከስድ ከመ ያዕሉ መጻሕፍተ ሥራይ ዘሀሎ ውስተ ኵኵሕ ዘጸሐፉ ረአይት ከመ ኢይደምሰስ በአይኅ… (cf. En69:9) (f. 9)*

ትርጉም፦ የጨረቃ ሩጫም በየዘመኑ፣ ጉድለቱም እንደ አውዱ እስኪተርፍ ድረስ የብርሃኑ መወለድም በጥንቃቄ እስኪሞላ ድረስ ከቀን ወደ ቀን እየተጨመረ። ሁሉም በቅድስት ሥላሴ ኃይል የተሰራ እና የተፈጠረ ነው።
ነፍሳትን ወደ ጥፋቱ የሚጠቅሰው መልአክ ይህ ነው። ሐሰትን ከእራሱ የሚያስተምር መልአክ ይህ ነው። ከሰው ልጆች ጋር ዝሙትን ፈፅመው ደመ ሥጋ እስኪወልዱ ድረስ የሰማይ ልጆችን አእምሮ የለወጠው መልአክ ይህ ነው። ረአይትን ሰውን እንዲገድሉ፣ በምድር ላይ ሥራይ እንዲያበዙ፣ በወፍ እንዲያሟርቱ ያደርጋቸው መልአከ ይህ ነው። አፍብድስን ረአይት የጻፉትን

በአላት ውስጥ ያለውን የአስማት መጽሐፍ በጥፋት ውሃ (በማየ አይኅ) እንዳይጠፋ እንዲያሸሽ ያደረገው መልአክ ይህ ነው።

ደራሲው በመጀመሪያው አንቀጽ ስለ ከዋክብት፣ ፀሐይ እና ጨረቃ ይናገራል። በየቀኑ በየወራቱና ዘመናቱ የሚወጡና የሚገቡ የከዋክብት አኗኗር በጥበበ እግዚአብሔር መዘጋጀቱን አባ ጊዮርጊስ ይገልጻል። በተጨማሪም የፀሐይ ምሕዋር፣ የጨረቃ በየጊዜው መመላለስ፣ ብርሃኑም ፈጽሞ እስኪሞላ ወይንም እስኪጎድል ድረስ ከዕለት ወደ ዕለት እንዴት እየጨመረ ወይንም እየቀነሰ እንደሚኼድ፣ በጠቅላላው ኹሉም ነገር በቅድስት ሥላሴ ኀይል እንደሚከናወን ያስረዳል።

በኹለተኛው አንቀጽ አባ ጊዮርጊስ ስለክፉው መልአክና መገለጫዎቹ ያብራራል። ከራሱ አመንጭቶ ውሸትን ለሌሎች የሚያስተምር፣ቃየል ወንድሙ አቤልን እንዲገድል ያስተማረ፣ የሰማይ ልጆችን (ደቂቀ ሴትን) ልቡናቸውን ወደ ዝሙት በመመለስ ከሰው ልጆች (ደቂቀ ቃየል) ጋር እንዲገናኙ ያደረገና ረአይት የተባሉ ረጃጅም ልጆችን እንዲወልዱ ያደረገ፣ በምድር ላይ ሰዎችን እንዲገድሉ፣ሥራይ ማድረግን በወፍ (በዶሮ) ማሟረትን እንዲለማመዱ ያደረገ ይኸ ክፉው መልአክ መሆኑን ከመጽሐፈ ሄኖክ በመጥቀስ ደራሲው ያብራራል።

## ፭.፮.ሄኖክ በመጽሐፈ ፀሐይ (Call No. EMML 1389)

መጽሐፈ ፀሐይ እንደ ስሙ ስለ ፍጥረታዊቷ ፀሐይ የሚያትት ሳይኾን ስያሜው ምሳሌያዊ (symbolical) ነው። ይኸውም ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጨለማ እንደ ሚገፈፍና እንደሚርቅ በፀሐይ የተመሰለ ቃለ እግዚአብሔርም ወደ ሰዎች አእምሮ በገባ ጊዜ በጨለማ የተመሰለ ድንቁርና ይወገዳል፤ ዕውቀት ጥበብ (ፈሪሐ እግዚአብሔር) ይገለጣል ለማለት መኾኑን ደራሲው ይናገራል። ደራሲው ከመጽሐፍ ቅዱስ በዋናነት ደግሞ ከትንቢተ ነቢያት ኀይለ ቃልን እየመዘዘ ግዕዝ በግዕዝ ያብራራል። ትርጓሜውን በምስክር ለማጽናት ሲሻም መጽሐፈ ሄኖክን እና ሌሎች መጻሕፍትን ዋቢ አድርጎ ይጠቅሳል። ለማሳሌ፡-

*"…ወዓዲ ይቤ ኢሳይያስ ከመ በኵረ ላህም ሥኑ ላህምሰ ይተረጎም በአዳም፤ ይቤ ሄኖክ በእንተ አዳም፡- ወጽአ ላህም ፀዓዳ እምድር (cf. En85:3) ወከመሰ ይመስሎ እግዚአብሔር ለአቡነ አዳም*

*ዳግመኛም ኢሳይያስም አለ ውበቱ እንደ በሬ አውራ ነው። በሬውም በአዳም ይተረጎማል። ሄኖክ ስለ አዳም አለ። ነጭ በሬ ከምድር ወጣ እግዚአብሔር አባታችን አዳምን እንደሚመስለው።*

*… ወዓዲ ይቤ ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ ወአድግኒ ምቅማሆ ወቤተ እግዚአ*

*(ኢሳ.1፡3)፤ አልህምትኒ አበው ቀደምት እሙንቱ እለ አእመርዎ ለእግዚአብሔር በከመ ሰመዮሙ ሄኖክ ወአእዱግሰ አሕዛብ እሙንቱ ወቤተ እግዚአሙኒ ቤተ ክርስቲያን ይእቲ እንተ ይቀምሁ በውስቴታ ትምህርተ ሃይማኖት። ሄኖክኒ ይቤ በእንተ አብርሃም ወእስማኤል፡- ወዝኩ ላህም ፀዓዳ ወለደ አድገ ገዳም፤ ላህምሰ ፀዓዳ አብርሃም ውእቱ ወአድግኒ እስማኤል..." (cf. En89:11)...(ff. 23-25)።*

*...ወዓዲ ይቤ ነቢይ ዕንባቆም፡- ወይትቀጠቀጡ አድባር እምኃይሉ ወይትመሰዉ አውግር ዘእምዓለም ርኢኩ...አድባርሰ ወአውግር እለ ተቀጥቀጡ ነገሥት ዓላውያን እሙንቱ። ወሄኖክኒ ይቤ በእንቲአሆሙ፡- ደብረ ሐፂን ወደብረ ጸሪቅ ደብረ ብሩር ወደብረ ወርቅ ደብረ ነጠብጣብ ወደብረ አረር እሉ ኩሎሙ በቅድሜሁ ለንሩይ ይከውኑ ከመ መዓረ ግራ ዘቅድመ እሳት፤ ወከመ ማይ ዘይወርድ እምላዕሉ ዲበ እሉ አድባር ወይከውኑ ድኩማነ በታሕተ እገሪሁ (cf. En52:6) ። እሉኬ ነገሥት አድባር እምዓለም እለ ይቀጠቅጥሙ ወልድ በዕለተ ስቅለቱ...*

*ትርጉም፡- ... ዳግመኛም አለ በሬ የገዥውን አህያም የጌታውን ጋጥ አወቀ (ኢሳ 1፥ 3)። ሄኖክ እንደሰየማቸው በሬዎቹ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ የቀደሙ አባቶች ናቸው። አሕያዎችም አህዛብ ናቸው። የጌታቸው ቤትም በውስጧ የሃይማኖት ትምህርትን የሚማሩበት (የሚግጡበት) ቤተ ክርስቲያን ናት። ሄኖክም ስለ አብርሃም እና ስለ እስማኤል ተናገረ። ይህ ነጭ በሬ የሜዳ አህያ ልጅ ነው። ነጩ በሬ አብርሃም ነው። አህያውም እስማኤል ነው ።*

*... ዳግመኛ ነብዩ እንባቆም አለ። ተራራዎች በኃይሉ ሲቀጠቀጡ፣ኮረብታዎችም ሲቀልጡ ለዘለዓለም አየሁ። የተቀጠቀጡ ተራራዎችና ኮረብታዎች ከሀድያን ነገስታት ናቸው። ሄኖክም ስለእነሱ ተናገረ የብረት ተራራ፣ የመዳብ ተራራ፣ የወርቅ ተራራ፣ የጠል ተራራ፣ የሐናር ተራራ እነዚህ ሁሉ በተመረጠው ፊት ከእሳት ፊት እንዳለ እንደ ግራር ማር ይሆናሉ። ከእነዚህ ተራራዎች እንደሚወርድ ውሃ ከእግሩ በታች ደካማ ይሆናሉ። እነዚህ ነገስታት ተራሮች ወልድ በሚሰቀልበት የሚቀጣቸው ናቸው።*

ከላይ እንደተቀመጠው በነቢዩ ኢሳይያስና ዕንባቆም የተጠቀሱትን ኀይለ ቃላት ለማብራራት የመጽሐፈ ፀሐይ ደራሲ ሄኖክን እንደምስክር ይጠራል። ለምሳሌ በኢሳይያስ የተነገረውን "...ላህምኒ አእመረ ዘአጥረዮ ወአድግኒ ምቅማሆ ወቤተ እግዚኡ/ በሬም ገዥውን አህያም ገለባ የሚቅምበትን የጌታውን ቤት አወቀ" የሚለውን ምሳሌያዊ ትምህርት ሲተረጉም አልህምት/በሬዎች የተባሉ እግዚአብሔርን የሚያውቁ/የሚያመልኩ አበው ሲኾኑ አእዱግ/አህዮች የተባሉት ደግሞ እግዚአብሔርን የማያወቁ/የማያመልኩ አሕዛብ መኾናቸውን ያመለክታል። እንዲኹም ገለባ የሚቅሙበት የጌታቸው ቤት የተባለችው ትምህርተ ሃይማኖትን የሚመገቡባት ቤተክርስቲያን መኾኗን መጽሐፈ ሄኖክን አብነት

አድርጎ ያስረዳል። ነቢዩ ዕንባቆም "ከነይሉ የተነሳ ተራሮች ይንቀጠቀጣሉ፤የዘላለምም ኮረብቶች እንደ ስም ይቀልጣሉ"[25] ሲል በተራሮች መስሎ ያስተላለፈውን ምሥጢር ከሄኖክ (52፡6) ከተነገረው ምሳሌ ጋር በማዛመድ በተራራና ኮረብታ የተመሰሉ ነገሥታትና መኳንንት መኾናቸውን ደራሲው ያብራራል። ይኸም ጌታ በስቅለቱ ሔሮድስ፣ ጲላጦስን፣ ሃና ቀያፋን እንዲሁም አጋንንትንና ሠራዊቱን ድል ማድረጉን ያመለክታል።

## ፩.፯.ሄኖክ በመጽሐፈ ስንክሳር (Call No. EMML 4273)

የመጽሐፈ ሄኖክ ጥቅሶች በስፋት ከሚገኙባቸው አንዱ መጽሐፈ ስንክሳር ሲኾን በተለይም ስለ ቅዱሳን መላእክት የሚያዘክረው ክፍል ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ መስከረም አንድ ቀን ስለ መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል፣ኅዳር ስምንት ስለ መልአኩ ቅዱስ አፍኒን እና አርባዕቱ እንስሳ፣ኅዳር12 ስለ ቅዱስ ሚካኤል፣ጥር 27 ስለ ነቢዩ ሄኖክ የተጻፉትን ማየት ይቻላል።

## ፪. መጽሐፈ ሄኖክ በግጥም ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ

ከግዕዝ ሥነ-ጽሑፍ አንዱ ዘውግ ግጥም ነው። አባቶቻችን ካወረሱን የሥነ-ጽሑፍ ቅርሶች መካከል ከማንም ያልተቀዳ የራሱ መሠረትና ቅርጽ ያለው ግጥም አንዱ ነው። የቅዱስ ያሬድ ድርሰቶችን ጨምሮ የእነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አባ ጽጌ ድንግል፣ አርከ ሥሉስ፣ ዘርዓ ያዕቆብ እና የመሳሰሉት ሊቃውንት ድረሰቶቻቸው በከፊል እንዲሁም በምልአት ግጥሞች ናቸው። መልክዕ፣ አርኬ፣ ነግሥ ተብለው ከሚታወቁት ባለ አምስት ስንኝ ግጥሞች[26] ባሻገር እንደ መስተብቁዕ፣ሊጦንና እሴብሕ ጸጋኪ የመሳሰሉ ባለ ብዙ ስንኝ ግጥሞችም አሉ።ሊቃውንቱ ለግጥሞቻቸው መነሻ ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከአዋልድ መጻሕፍት በቀጥታም ኾነ በተዘዋዋሪ የሚወስዱ ሲኾን መጽሐፈ ሄኖክንም እንደ ምንጭ ተጠቅመውበት እናገኛለን። ጸሓፍያኑ መጽሐፈ ሄኖክን መነሻ አድርገው በደረሷቸው ግጥሞች ትምህርተ ሃይማኖትን (ነገረ ሥላሴ፣ ነገረ ክርስቶስ፣ ነገረ ማርያም፣ነገረ መላእክትን ወዘተ) በስፋትና በጥልቀት አስተላልፈዋል።ኹሉንም ማቅረብ ባይቻልም ለምሳሌ ይኾን ዘንድ የሚከተሉትን እንመልከት።

---

[25] ዕንባቆም 3፡6

[26] እዚኽ ላይ የግጥምን ባሕርያት (የቃላት ምርጫና ምጠና፣ የቤት መምታትና መድፋት ወዘተ) አሟልተው ስለሚገኙ ግጥም ተባሉ እንጂ መልክእ፣ አርኬ ነግሥ የራሳቸው መለያ ሥነ-ጽሑፋዊ ባሕርይ ያላቸው መኾኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

በከመ ሄኖክ ዜነወነ ነኵርኳረ ነፋስ ዘተጽዕነ
ልሣነ እሳት ሕኑጽ ዘትረፍቅ መካነ
ጸራቅሊጦስ ነድ ቁርባነ ምሥጢር ዘኮነ
ክረምተ ሕግከ ነፍንፍ ዲቤነ
አስካለ ወንጌል ስሂነ ዘያፈሪ ብነ።

ምንጭ:- አርኬ፡ Call No EMML3128,f 7 , date: 16th cent

ትርጉም፡ በነፋስ ሠረጋላ የተጫነ /የተጓዘ ሄኖክ እንደነገረን
በእሳት ልሣን በታነጸ ቤት
የምትኖር ጸራቅሊጦስ ነድ ሆይ፣ የሚስጥር ቁርባን የኾነ
ክረምት ሕግህን በእኛ ላይ አዝንም፤
የወንጌል ዘለላ (ፍሬን) በእኛ ያፈራ ዘንድ፡

ከላይ ያለው ግጥም ዋና ሐሳቡ ጸራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን የሚያመሰግን ሲኾን ገጣሚው ለሐሳቡ መነሻ ያደረገው ነቢዩ ሄኖክ ያየውን ምሥጢር ነው። ይኸውም በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 14፡15-22 የተከተበው ሲኾን የሚከተለው ነው፡-

*…ወናሁ ካልዕ ቤት ዘየዐቢ እምዝንቱ ቤት ወኵሉ ኆኅቱ ርኅው በቅድሜየ ወሕኑጽ በልሳነ እሳት። ወበኵሉ ይፈደፍድ በስብሐት ወበክብር ወበዕበይ እስከ ኢይክል ዜንዎተክሙ በእንተ ስብሐቲሁ ወበእንተ ዕበዩ። ወምድሩሰ እሳት ወመልዕልቴሁ መብረቅ ወምርዋጸ ከዋክብት ወጠፈሩኒ እሳት ዘይነድድ። ወነጸርኩ ወርኢኩ ውስቴቱ መንበረ ልዑለ ወራእዩ ከመ አስሐትያ ወክበቡ ከመ ፀሐይ ዘያበርህ ወቃለ ኪሩቤል። ወእምታሕተ መንበሩ ዐቢይ ይወፅኡ አፍላገ እሳት ዘይነድድ ወኢይክሉ ርእዮቶ። ወዐቢየ ስብሐት ይነብር ላዕሌሁ ወዐጽፋሰ ዘይበርህ እምፀሐይ ወይጸዐዱ እምኵሉ በረድ። ወኢይክል መኑሂ እመላእክት በዊአ ወራእየ ገጹ ለክቡር ወስቡሕ ወኢይክል መኑሂ ዘሥጋ ይርአይ ኪያሁ እሳተ። እሳት ዘይነድድ በዐውዱ ወእሳት ዐቢይ ይቀውም ቅድሜሁ ወአልቦ ዘይቀርብ ኀቤሁ እምእለ ዐውዱ ትእልፊተ ትእልፊት ቅድሜሁ ወውእቱስ ኢይፈቅድ ምክረ ቅድስተ…*

*ትርጉም፡- … አሁን ከዚህ ቤት የሚበልጥ ሌላ ቤት ሁሉም በሮቹ በፊቴ ተከፈቱ። በእሳት ልሳን የታነፀ ነው። ስለ ምስጋናው እና ግርማው ልነግራችሁ እስከማልችል ድረስ ክብሩ ምሥጋናው፣ ግርማሞገሱ ከሁሉም ይልቃል። ታች እሳት ላዩ መብረቅ ከዋክብት የሚሮጡበት። ጣራውም የሚነድ እሳት ነው። በውስጡ መልኩ እንደ አመዳይ፣ ክበቡ በኪሩቤል ቃል እንደሚያበራ ፀሐይ ያለ ታላቅ ዙፋን (መንበር)*

*አየሁ። ከታላቁ ዙፋን በታች ለማየት የማይችሉ የሚነዱ የእሳት ወንዞች ይወጣሉ። ታላቅ ምስጋና ከላዩ ላይ ተቀምጧል። መጎናፀፊያው ከፀሐይ ይልቅ ይበራል። ከበረድም ሁሉ ይነጣል ከመላእክት ማንም መግባትና የተነሰገነውን፣ የተከበረውን ገፁን ማየት አይችልም። ከሥጋዊውም ማንም እሱን እሳትን ያይ ዘንድ አይችልም። በዙሪያው እሳት ይነዳል። ታላቅ እሳትም በፊቱ ይቆማል በዙሪያው ካሉ የብዙ ብዙ በፊቱ የሚቀርብ የለም። እሱም የተለየች ምክርን አይሻም……*

ከላይ እንደተመለከትነው በእሳት ላንቃ በታነጸው፣ሊነገርና ሊተረጎም በማይችል በክብር ሁሉ ከፍ ያለ ቤት፣ መሠረቱ እሳት፣ ጠፈሩ እሳት፣ በላዩም የከዋክብትና የመባርቅት መፋጠን የሚታይበት ቤት ውስጥ ሌላ ደግሞ እጅግ ከፍ ያለ፣ መልኩ እንደ ዐመዳይ፣ ክበቡ እንደ ፀሐይ የሚያበራ፣ከሥሩም የሚነድ የእሳት ወንዞች የሚፈልቁበት መንበር እንደ አየ ይገልጻል።

በዚኽም መንበር ላይ የክብርና የምስጋና ባለቤት፣መጎናጸፊያው ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ፣ ከበረዶም ኹሉ የሚነጣ፣ ከመላእክትም ወገን ማንም ወደርሱ መቅረብ የሚቻለው የሌለ፣ "ወኢይክል መኑሂ ዘሥጋ ይርአይ ኪያሁ እሳተ "- ከሥጋውያን ፍጥረታትም ወገን ማንም ሊያየው የማይችል "እሳት" ተብሎ የተጠራ ተቀምጦበታል። ይኽንን ነቢዩ ሄኖክ "እሳት" ብሎ የጠራውን ምሥጢር ደራሲው "ጰራቅሊጦስ ነድ" በማለት በዚያ ግሩምና ድንቅ በኾነው ቤትና በሚያስፈራው መንበር ላይ የተገለጸው መንፈስ ቅዱስ መኾኑን ተርጉሞልናል።

ከሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት በተለይም በሐዲስ ኪዳን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ኹለት አንጻርም ሲታይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል መገለጡ የተለመደ በመኾኑ[27] ደራሲው የሄኖክን ምሥጢር ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶ መተርጎሙ የትኛውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ ሊያስማማ የሚችል ሀቅ ነው። በመኾኑም ሊቁ ደራሲ መጽሐፈ ሄኖክ በነገረ መንፈስ ቅዱስ (Pnuemathology) ላይ ሊኖረን የሚገባንን ዕውቀት እንድናገኝና ልናደርገው የሚገባንን ጥናትና ምርምር ለማሳደግ የሚያግዘን ኹነኛ መጽሐፍ መኾኑን አመላክቶናል።

ወመጽአ ኀቤየ ርእሰ መዋዕል
ሄኖክ ይብል
ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል
ወምስለ ሩፋኤል ወፋኑኤል

---

[27] ለምሳሌ ማቴ. 3፡11 (*ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው (በአንድምታ)*፣ (1988 ዓ.ም)፣ አዲስ አበባ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ምስለ ኵሎሙ አዕላፈ አዕላፋት
እለ አልቦሙ ኍልቊ ሠራዊት
ምንጭ:- ነግሥ/ እግዚአብሔር ነግሠ Call No. 7061, f6, date:15thcent.

ሄኖክ እንዲህ አለ፡- ብሉየ መዋዕል (አብ)
ወደእኔ መጣ፤ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር፤
ከሩፋኤልና ከፋኑኤል ጋር፤
ቁጥር ከሌላቸው የብዙ ብዙ ከሚሆኑ ሠራዊተ
መላእክት ጋር።

የዚኽም አርኬ መሠረተ ሐሳብ "...ወመጽአ ውእቱ ርእሰ መዋዕል ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ሩፋኤል ወፋኑኤል ወአእላፍ ወትእልፊተ አእላፍ እለ አልቦሙ ኍልቍ..." (ሄኖክ.71፥13) ከሚለው በቀጥታ የተወሰደ ነው። የግጥሙ ዋና መልእክትም ብሉየ መዋዕል ተብሎ የሚጠራ ዘመን የማይቆጠርለት እግዚአብሔር እልፍ አእላፋት በኾኑ መላእክት ታጅቦ እርሱ በወደደው መጠን ለሄኖክ መታየቱን ወይም መገለጡን ያስረዳል። ምንም እንኳ ሠለስቱ አካላት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ብሉየ መዋዕልነት ገንዘባቸው ቢኾንም በመጽሐፈ ሄኖክ አገባብ ግን ብሉየ መዋዕል የሚለው አገላለጽ በአብዛኛው የሚያመለክተውከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር አብን ነው። ለምሳሌ፡- "ወበህየ ርኢኩ ዘሎቱ ርእሰ መዋዕል፤ ወርእሱ ከመ ፀምር ፀዓዳ፤ ወምስሌሁ ካልዕ ዘገጹ ከመ ርዕየተ ሰብእ... ወተስእልክዎ ለአሐዱ እመላእክት ቅዱሳን ዘየሐውር ምስሌየ ወኵሎ ኅቡአተ ዘአርአየኒ በእንተ ዝኩ ወልደ ሰብእ"[28] (መ.ሄኖክ ትርጓሜ 12፥19) በሚለው ገጸ ምንባብ ውስጥ **ዘሎቱ ርእሰ መዋዕል** የሚለው ሐረግ የሚወክለው ብሉየ መዋዕልነት ገንዘቡ የኾነ እግዚአብሔር አብን ሲኾን ከርሱ ጋር አብሮ ለሄኖክ የተገለጠውና **ዘገጹ ከመ ርዕየተ ሰብእ፣ ወልደ ሰብእ** ተብሎ የተጠራው እግዚአብሔር ወልድ ነው። ይኸውም ወልደ አብ የተባለ የአካላዊ ቃልን ደኃራዊ ልደቱንና ሰው መኾኑን አስቀድሞ ለሄኖክ በምሥጢር እንደገለጠለት የሚጠቁም ነው። በመኾኑም ከላይ ያለው ግጥም (ነግሥ) መጽሐፈ ሄኖክ ስለ እግዚአብሔር አብ የሚያስተምር መኾኑን ያስረዳል።

ሰላም እብል ለሄኖክ ጸሐፊሁ
ሙፃዓ ትንቢት እምቅድሜሁ
እምአዳም አቡሁ ወእስከ ክርስቶስ ጌናሁ
ወልደ ሰብእ ይመስል ርኢክዎ ይብል
በመንበረ ስብሐት ግሩም እንዘ ይነብር ኀይል።
ምንጭ:- እግዚአብሔር ነግሠ Call No. 7061, f 50

[28] ሄኖክ 12:19 (*መጽሐፈ ሄኖክ (አንድምታ)፤* (2003 ዓ.ም)፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ከአባቱ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ
ትንቢትን ለተናገረ ለጸሓፊው ሔኖክ ሰላምታ አቀርባለሁ፡፡
(እንዲህም) አለ፡- ድንቅ በኾነ የክብር ዙፋን ላይ ተቀምጦ
ኃይልን (ወልድን) አየሁት፤ የሰውን ልጅ ይመስላል፡፡

የዚኽ አርኬ ዋና ዓላማ የወልደ እግዚአብሔር ሰው የመኾን ምሥጢር አስቀድሞ የተገለጠለትና ይኽንን ለጻፈ ለነቢዩ ሄኖክ ሰላምታ/ምስጋና ማቅረብ ሲኾን መነሻ ሐሳቡም፡- በምዕራፍ 46፥47 እና 48 ላይ ሄኖክ ከአዳም ጀምሮ እስከ ክርስቶስ እንዲሁም እስከ ዳግም ምጽአተ ክርስቶስ በምሳሌ የተናገረውን መሠረት ያደረገ ሲኾን በተለይም ነገረ ክርስቶስን በሰፊው ያስረዳል፡፡ በመኾኑም ደራሲው ይኽንን ነገረ ክርስቶስን (Christology) በጥልቀትና በስፋት ለመማር ትልቅ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችል መጽሐፍ ለጻፈልን ለሄኖክ የምስጋና ሰላምታ ሲያደርስለት እናያለን፡፡ እስካሁን ለአብነት ባቀረብናቸው ድርሳናት ውስጥ እንዳየነው መጽሐፈ ሄኖክ ስለ ነገረ ሥላሴ ጥናት (Trinitarian Theology) ይልቁንም ስለ ነገረ መንፈስ ቅዱስ እና ነገረ ክርስቶስ ሊያስተምረን የሚችለው ብዙ ነገር መኖሩን ተገንዝበናል፡፡ በነገረ ማርያም ጥናት (Mariology) ዙሪያም ቢኾን ከመጽሐፈ ሄኖክ ብዙ ነገር መማርና ማጥናት እንደሚቻል የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት ጥልቅና የታመቀ ምሥጢር በላቸው ድርሰቶቻቸው አሳይተውናል፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን ማየት በቂ ነው፡፡

ሰላም ለማርያም ቤተ ሄኖክ ነቢይ
በምድር ሐዋዝ ሥነ ሕንፄሃ ዐባይ
ወሥነ ሡራሬሃ ያበርህ እምሥነ ፀሐይ
ፈለሰት ይእዜ ከብካበ ሰማይ
ተማኅፀነ ባቲ እምኵሉ እኁይ፡፡

ምንጭ፡- ነግሥ (Call No. 3592, f10, date: 18th cent

በመልካም ምድር ላይ የሕንፃዋ ውበት ታላቅ የኾነ፣
የአሠራሯም ውበት ከፀሐይ ይልቅ የሚያበራ
የነቢይ ሄኖክ ቤት ለተባለች ለማርያም ሰላምታ ይገባል፡፡
ወደ ሰማያዊ የሰርግ አዳራሽ ዛሬ አረገች፤
ከክፉ ኹሉ ታድነን ዘንድ በእርሷ እንማጸናል፡፡

የድርሰቱ ዋና መልእክት ነቢዩ ሄኖክ በራእይ ባያት ቤት የተመሰለቸው ድንግል ማርያም መኾኗንና ነገረ እርገቷ ላይ የሚያተኩር ሲኾን መሠራታዊ ሐሳቡም የተወሰደው ከመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 90 ቁጥር 27 ነው፡፡ በዚኽ ራእዩ ሄኖክ በመልካም ምድር ላይ የተሠሩ ኹለት ቤቶችን በቅደም ተከትል ወይም ተራ በተራ (አንዱ ፈርሶ ሌለው ሲተካ) የተመለከተ

ሲኾን የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ የትርጓሜ መጻሕፍት ሊቃውንት እነዚኽን ቤቶች፡- በሕገ ኦሪትና በሕገ ወንጌል፣ በምኩራብና በቤተ ክርስቲያን ምሳሌነት እንደ ቅደም ተከተላቸው ተርጉመዋቸዋል።

ከላይ ባላው አርኬ ውስጥ ግን ደራሲው ቤተ ሄኖክ የተባለች ድንግል ማርያም ናት የሚል ሲኾን እንዲኹም ሄኖክ ባያት ቤት ሲመስላት ከዚያች ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸውና በነቢዩ የተነገሩት ኹሉ እርሷንም የሚመለከቱ መኾናቸውን እያሰበ በመኾኑ ወደምሳሊያዊ ትንታኔው ከመሄዳችን በፊት እነዚኽን ነገሮች ማየቱ ተገቢ ነው። በመኾኑም ሄኖክ ያያት ቤት ምን ትመስል ነበር? ስንል፡-

- ይኽችን ቤት ያመጣት የበጎች እረኛ ነው።
- "ምድር ሐዋዝ" (ያማረ ምድር) ላይ የተመሠረተች ናት።
- ከመጀመሪያዋ ቤት የበለጠ ውበቷ ኹለመናዋ አዲስና ታላቅ ነው።
- ምሰሶወቿ ኹሉ አዳዲስ ናቸው።
- በውስጧም የበጎች እረኛ የተቀመጠበት ዙፋን አለ።

እነዚኽን ነጥቦች መሠረት አድርገን ከላይ ደራሲው ስለ ለገረ ማርያም ሊያስተምረን የፈለገውን ብንመለከት እጅግ በጣም ሰፊና ጥልቅ ኾኖ እናገኘዋለን። በመጀመሪያ ድንግል ማርያምን በቤት መስሎ ማቅረቡ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይትበሀል አንጻር "ቤት" የሚለው ቃል " ሰው፣ ሰውነት" የሚለውን ሐሳብ ወክሎ የሚነገር በመኾኑ አማናዊ ምሳሌነቱን መገንዘብ ይቻላል[29]።

"ምድር ሐዋዝ" ተብላ የተገለጸቸው ያች ቤት የተሠራችበትን ቦታም አማናዊት ቤተ መቅደስ የተባለች ድንግል ማርያም የተፀነሰችበትን ማኅፀነ ሃናን ይመለከታል። ይኽንንም አገላለጽ አባቷ ቅዱስ ዳዊት "መሠረታቲሃ ውስተ አደባር ቅዱሳን"[30] (መዝ. 87፥1) ካለው ጋር ተዛማጂ መኾኑን ልብ ይሏል። ሃናም "ምድር ሐዋዝ" ተብላ መጠራቷ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ባማረና በተቀደሰ አኗኗር ትገኝ ስለነበር ነው።
ይኽች ቤት ከመጀመሪያዋ ቤት እንደምትበልጥ መነገሩ፣ ድንግል ማርያም ከእነ ሔዋን፣ ከነ ሣራ፣ርብቃ በጠቅላላው ከቅዱሳት አንስት የምትበልጥ መኾኗን ሲያስረዳ ነው ።

[29] 2ኛ ነገ. 20፥1፤ ዮሐ. 2፥19።

[30] መዝ. 87፥1 (*መዝሙረ ዳዊት ንባቡና ትርጓሜው፣*(1982)፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት።

ይኽንም እውነታ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ "አንቲ ተዐብዪ እምብዙኃት አንስት እለ ነሥአ ጸጋ ወክብረ" ሲል በግልጽ መስክሮላታል፡፡ በዚች ቤት ውበቷ ሁለመናዋ አዲስ ነው መባሉም ድንግል ማርያም በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋዋ፣ በኀልዮ፣ በነቢብ በገቢር ንጽሕት እንደኾነች ያጠይቃል፡፡ ደራሲው "በምድር ሐዋዝ ሥነ ሕንጼሃ ዐባይ" በሚለው ስንኙ ድንግል ማርያም በእናቷ ማኅፀን ስትፀነስ ጀምሮ ከጥንተ አብሶ ንጹሕ በኾነ መንገድ መኾኑን ያስረዳናል፡፡ በዚች ቤት ውስጥ ያሉት ምሰሶዎች አዲሶች ናቸው የሚለው አገላለጽ ድንግል ማርያም በነፍሷም በሥጋዋም ኹል ጊዜ አዲስ ናት፤ በኹለት ምሰሶዎች በሚመሰሉት በድንጋሌ ሥጋ ወነፍስ በዘለዓለማዊ ሕዳሴ ውስጥ ተጠብቃ የምትኖር መኾኗን እንድናስብ ያመላክተናል፡፡ በተጨማሪም በዚች ቤት ውስጥ የበጎች እረኛ የተቀመጠበት ዙፋን መታየቱ ኖላዌ አባግዕ[31] ተብሎ የሚመሰገን ክርስቶስ ለዙፋንነት የመረጠው ማኅፀነ ማርያም መኾኑ የታመነ ነው፡፡ ይኽችን ቤት "ምድር ሐዋዝ" በተባለች ቦታ የሠራት የበጎች እረኛ እንደኾነ መገለጹ፣ድንግል ማርያምን በማኅፀነ ሃና አስቀድሞ ያዘጋጀ፣ ለእናትነት የመረጠ እውነተኛው የበጎች እረኛ ሰው የኾነ አምላክ መኾኑን እንረዳለን፡፡ በዚኽም ድንግል በማኅፀኗ የፀነሰቺውና በድንግልና የወለደችው ፈጣሪዋን መኾኑን፣ አንድም ከድንግል ማርያም የተወለደው ቅድመ ዓለም የነበረ ፈጣሬ ዓለማት መሆኑን እንድንረዳና ጥልቅ ወደኾነው ወደ ነገረ ሥጋዌ ዐይነ ልቡናችንን እንድናቀና ይጋብዘናል፡፡

በመጨረሻም ከላይ ባለው ግጥም የመዝጊያ ስንኞች ላይ እንደምንረዳው ቤተ ሄኖክ ተብላ የተጠራች ድንግል ማርያም ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም መሸጋገሯን ነው፡፡ እርሷ አኹን ያለችበትንም ዓለም "ከብካበ ሰማይ- በሰማይ ያለ የሰርግ አዳራሽ" በማለት የገለጸው ሙሽራው ክርስቶስ ባለበት ሙሽራዪቱ ድንግል ማራይም በሰርግ አዳራሽ በተመሰለች በመንግሥተ ሰማይ የምትኖር መኾኑዋን ያስረዳል፡፡ ይኽም አገላለጽ ነቢዩ ዳዊት ሙሽራውና ሙሽራይቱን በንጉሥና በንግሥት መስሎ "ወትቀውም ንግሥት በየማንከ በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኁብርት"[32] በማለት የዘመረላትን መዝሙር ያስታውሰናል፡፡

## ፯. መጽሐፈ ሄኖክ በቅኔ ውሥጥ

የቅኔ ሊቃውንት መጽሐፈ ሄኖክን የቅኔዎቻቸው የሐሳብ ምንጭ፣ የምሥጢር ማፍለቂያ አድርገው ተጠቅመውበታል፡፡ ይኽንም የሚያስረዱ ብዙ ቅኔዎች ቢኖሩም በዚኽ ክፍል

[31] የሐ. 10፥1-18

[32] መዝ. 45፥9

ግን ኹሉንም ማቅረብ ስለማይቻል ለምሳሌ ይኾነን ዘንድ የሚከተለውን ቅኔ እንመርምር፡

*ኢያስተፍሥሕዎ ነዳያን*
*ሙሴ ወኖኅ ለዘመደ ሥጋ ልደት*
*ጽውመ እስመ አኅደርዎ በብርሃን ቤት*
*ባዕለ ጸጋሰ ወልድ አክባሬ ልደት ብሑት*
*እስመ ምስለ መዓር አቅረበ ሀሊብ ሕይወት*
*ወኅብስተ ዘአልቦ መስፈርት*[33]::

*ነዳያን የኾኑ ሙሴና ኖኅ የሥጋ ዘመድ ልደትን*
*አላደሰቱትም፤ በብረሃን ቤት ጦሙን አሳድረውታልና፡፡*
*ባለጸጋ ወልድ ግን ልደትን የሚያከብር የሠለጠነ ነው፡፡*
*የሕይወት ወተትን ከማር ጋር አቅርቧልና፡፡*
*ሥፍር ቁጥር የሌለው ኅብስትንም (አቅርቧልና)፡፡*

ይኽ ቅኔ ዋዜማ በመባል የሚታወቅ ባለ አምስት ስንኝ ቅኔ ሲኾን ቅኔው የተደረሰውም ኢትዮጵያዊ ባህልንና የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክን በማቀናጀት ነው፡፡ በባህላችን እንግዳን ተቀብሎ ያለው ማሩን ቅቤውን ወተቱን ዳቦውን አቅርቦ የሌለው ደግሞ ቤት ያፈራውን አቅርቦ የሚያስተናግድ ከኾነ ያሰው ቸር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ሰው አክባሪ ነው ይባላል፡፡ ይኽን የማያደረግ ከኾነ ደግሞ ንፉግ፣ ክፉ መባል አይቀርለትም፡፡

ባለቅኔው ይኽንን ሰም ተጠቅሞ ኖኅንና ሙሴን ከክርስቶስ ጋር በማነጻጸር እነርሱ በእንግዳ የተመሰለ ልደትን (መወለድን) በአግባቡ እንዳልተቀበሉት፣ በብርሃን ቤታቸው ጦሙን እንዳሳደሩት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ማሩን ወተቱን፣ ዳቦውን እንዳቀረበለትና በክብር እንደተቀበለው ይናገራል፡፡

ወደ ቅኔው ወርቅ ወደ ኾነውና ወደዋናው ወደተነሣንበት መልእክት ስናልፍ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክን እንድናስተውል ይጋብዘናል፡፡ ይኸውም በቅኔው የተጠቀሱት ጻድቁ ኖኅና ነቢዩ ሙሴ ሲኾኑ በብርሃን ቤታቸው ልደት እንግዳን ጦም አሳደሩት ማለት እነርሱ በተወለዱበት ዕለት ቤታቸው (የዘመዶቻቸው ቤት) ተአምራዊ በኾነ ብርሃን ተሞልቶ እንደነበር ባለቅኔው በምሥጢር መናገሩ ነው፡፡ በኖኅ የልደት ቀን የተከናወነውን ተአምራዊ ክስተት በተመለከተ መጽሐፈ ሄኖክ እንዲኽ ይላል፡-

[33] *የግዕዝ ቅኔያት የሥነ ጥብብ ቅርስ፣ ንባቡ ከነ ትርጓሜው፣ቅጽ 3፣ገጽ 89፣(ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ)፡፡*

*…ወእምድኅረ መዋዕል ነሥአ ወልድየ ማቱሳላ ለወልዱ ላሜህ ብእሲተ ወፀንሰት እምኔሁ ወወለደት ወልደ። ወኮነ ሥጋሁ ጸዐዳ ከመ አስሐትያ ወቀይሕ ከመ ጽጌ ረዳ፤ ወጸጒረ ርእሱ ከመ ፀምር ጸዐዳ፣ ወድምድማሁ ወሠናይ አዕይንቲሁ። ወሶበ ከሠተ አዕይንቲሁ አብርሃ ኵላ ቤተ ከመ ፀሐይ ወፈድፋደ በርሀ ኵሉ ቤት። ወሶበ ተንሥአ እምእዴሃ ለመወልዲት ከሠተ አፉሁ ወተናገረ ስብሐቲሁ ለእግዚአ ጽድቅ። … ወፈርሀ ላሜህ አቡሁ እምኔሁ ወጐየ ወመጽአ ኀበ አቡሁ ማቱሳላ። ወይቤሎ አነ ወለድኩ ወልደ ውሉጠ ወኢኮነ ከመ ሰብእ ወይመስል ደቂቀ መላእክተ ሰማይ ወፍጥረቱ ካልዕት ወኢኮነ ከማነ፤ ወአዕይንቲሁ ከመ እገሪሁ ለፀሐይ ወገጹ ስቡሕ…(ሄኖክ 106፥1-5)*

*ትርጉም፡- … ከዘመናት በኋላ ልጅ ማቱሳላ ለልጁ ሚስት ወሰደ። ከእርሱም ፀነሰች፣ ልጅም ወለደች። ሥጋው እንደ አመዳይ ነጭ፣ እንደ ጽጌረዳ ቀይ ሆነ። የእራሱ ፀጉርም እንደ ነጭ ግምጃ ነው። ቅንድቡና ዓይኖቹ ጥሩ ናቸው። ዓይኑን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እነደ ፀሐይ አበራው። ቤቱ ሁሉ ፈጽሞ በራ። ከአዋላጅቱ በተነሳ ጊዜ አፉን ከፈተ፣ ምስጋና ለእውነት ጌታ ብሎ ተናገረ። … አባቱ ላሜህ ፈራ፣ ከእሱም ሸሸ። ወደ አባቱ ወደ ማቱሳላም መጣ ። ለአባቱም አለው የተለየ ልጅ ወለድኩ። እንደሰው አይደለም። የሰማይ መላእክት ልጅ ይመስላል አፈጣጠሩም የተለየች ናት። እንደኛ አይደለም ዓይኖቹ እንደ ፀሐይ እግሮች ናቸው ፊቱም ብሩሕ ነው (ሄኖክ 106፥1-5)*

ነቢዩ ሙሴ በተወለደ ጊዜም እንዲኹ ተመሳሳይ ታሪክ እንደነበረው መተርጕማነ መጻሕፍት ያስረዳሉ[34]። ይኹን እንጅ በነዚኽ በኹለቱ አባቶች የልደት ቀን ማርና ወተት፣ ዳቦም አልቀረበም። በኢየሱስ ክርስቶስ የልደት ቀን ግን የተወለደባት ቦታ ቤተ ልሔም በብርሃን ከመሞላቷ ባሻገር[35] ወንዞች ወደ ወተትና መዓር፣ ተራሮችም ወደ ኅብስት እንደ ተቀየሩ ትውፊት ያስረዳል። ይህንኑ የዜማው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ "በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ አድባር ኮኑ ኅብስተ ሕይወት፡ ወዕፀወ ገዳምኒ ፈረዩ አስካለ በረከት፤ ማየ ባሕርኒ ኮነት ሐሊበ ወመዓረ…"[36]በማለት በልደት ዝማሬው አካቶታል።

# ፰. ማጠቃለያ

በዚኽ ጥናታዊ ጽሑፍ ውስጥ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው መጽሐፈ ሄኖክ በግዕዝ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍ እና በቅኔ ውስጥ በጣም ሰፊ ቦታ ይዞ የሚገኝ ነው። ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በስፋት አጥንተውታል፤ ተርጕመውታል፤ ተመራም

[34] ዘፀ. 2፥2 (መጻሕፍተ ብሉያት ፬ቱ እሉ እሙንቱ ኦሪት ዘፍጥረት (ዘልደት) ኦሪት ዘፀአት (አንድምታ ትርጓሜ)፣ . (1999)፣አዲስ አበባ፣ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።
[35] ሉቃ. 2፥9
[36] ያሬድ (ቅዱስ)፣ (1986)፣ *ዝማሬ መዋሥዕት፣* አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት።

ረውበታል። ነገረ እግዚአብሔርን፣ ነገረ-ማርያምን፣ ነገረ-መላእክትን ለመማርና ለማስተማር በጽሑፎቻቸው ውስጥ ጠቅሰውታል። እንዲኹም ስለ ሥነ-ፍጥረት (ስለ ፀሐይ፣ጨረቃ እና ከዋክብት)፣ስለ መልክዓ ምድር (ለምሳሌ የገነት መገኛ አቅጣጫ)፣ ልዩ ልዩ መዓዛ ስላላቸው ዕፅዋት ወዘተ ለመግለጽ ሊቃውንቱ መጽሐፈ ሄኖክን ተጠቅመዋል። በተጨማሪም ሰዎች ከክፉ ሥራ (ለምሳሌ ከጥንቆላና ከሟርት) እንዲርቁ አስተምረውበታል።

ይኹን እንጂ ይኽንን ብርቅየ የኾነ የሀገራችን ብሎም የዓለማችን የሥነ-ጽሑፍ ሀብት የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሊቃውንት እንዴት እንዳጠኑት የሚያሳይና ላሁኑ ዘመን ትውልድ ለማስተዋወቅ የሚደረግ ሳይንሳዊ የጥናት ትኩረት በተገቢው ደረጃ ያገኘ አይመስልም። ይልቁንም በተዛማጅ ሥራዎች ዳሰሳ ላይ እንደተገለጸው የመጽሐፉ ይዘት ያልገባቸውና ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች መጽሐፉን የጥንቆላና የኮከብ ቆጣሪዎች (ሟርተኞች) መጽሐፍ አድረገው ሲቆጥሩት ይታያል። ከዚኽም አልፈው የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ደምራ የክብር ቦታ የሰጠችው ትምህርተ ሃይማኖት ስለሚያንሳትና የቀኖና መጻሕፍትን መለየት ስለማትችል ነው ብለው በድፍረት ጽፈዋል። ይኽ ግን ፍጹም ስሕተት ነው። ስለ ነገረ እግዚአብሔር፣ ነገረ ማርያም፣ ነገረ መላእክት ምሥጢራተ ብርሃናትንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊም ኾነ ዓለማዊ ዕውቀቶችን የያዘን መጽሐፍ እንደ ኢምንት ከመቁጠር ይልቅ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ማጥናትና መመርመር አስፈላጊ ነው ብየ አምናለሁ።